እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!!



ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን ።
ክርስቶስ ተነሣ ከሙታን በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ።

# ትንሣኤ



ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ሲሄድ ፡ ለሚያለቅሱ ሴቶች ለራሳችሁ እንጂ ስለኔ አታልቅሱ እንዳላቸው ።

መጋቢት ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጐምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


# ማውጫ

አርእስት — ገጽ


ደብዳቤዎች ............ ፩
ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ ለማን ታየ? ............ ፪
፲፫ ሕማማተ መስቀል ............ ፫
ይህን ያውቁ ኖሯል? ............ ፬
ሊቃውንቶቻችን ............ ፭
ሰባቱ ነገራተ መስቀል ............ ፮
ዓለም አቀፋዊ የጥናት ጉባኤ ............ ፰
ሰሙነ ሕማማት ............ ፲
ድንኳን ሰፊዋ ወይዘሮ ............ ፲፩
ዜና አብያተ ክርስቲያናት ............ ፲፪
ምን እንርዳዎ? ............ ፲፫
የሃይማኖት ዐምድ ............ ፲፬
ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ ............ ፲፭
ወጣት በሰበካ ጉባኤ ............ ፲፰
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............ ፲፱
ስለ ኢትዮ . ኦ . ተ . ቤ. ክ . በአፍሪካ አዳራሽ ............ ፳
የጤና ዐምድ ............ ፳፩
ትንሣኤሙታንን እናምናለን ............ ፳፪
የመጽሐፍ ቁዱስ ዐምድ ............ ፳፬


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

1ኛ ከአባ ተክለ ድንግል ደሴ በቁጥር 21 ፤ 2ኛ ከወረታ ለማ በቁጥር 24ላይ የተጻፈውን ተመልክቻለሁ ። አባ ተክለ ድንግል ደሴ ቤተ ክርስቲያናችን በሱባኤ ነቢያት ። በቀመረ ሊቃውንት መነሻና መድረሻ ያለው አቆጣጠር አላት ። ይኸውም እስከ ልደተ ክርስቶስ እስከ ምጽአተ፡ እያለች 8 ሺህ ትቆጥራለች ብለው ያስተላለፉት መልእክት የነቢያት ሱባኤና የሊቃውንት ቀመር አይደለም ። ምክንያቱም ተጣርቶ መታወቅ ያለበት ትምህርት ነው ይባላል እንጂ አላት እያሉ የሚታለፍ ትምህርት አይደለም ። ይህም ይታወቅ ዘንድ ዘመኑ አዳም አባታችንና ሔዋን እናታችን ከገነት ከወጡ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ 7472 ሆኗል እንላለን ። ይህንንም በሱባኤ ነቢያትና በቀመረ ሊቃውንት ሲቆጠር 4 መቶ ስንኳ አልሞላም ። 2ኛ አባ ተክለ ድንግል ደሴ እኔንም ሆነ የሊቃውንት ጉባኤና በየክፍሉ ሀገሩ ያሉ የቁጥር ሊቃውንት ሲጠየቁ ትክክለኛውን ቁጥር አውቆ ለማሳወቅ የሚረዳ ነው ብለው እንደሆነ ዳኘነቱ የግል ሐሳባቸው ነው ። ግን ጥያቄያቸው መምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ከ1971 ዓ.ም. ጀምሮ ወደፊት 2642 ዓመታት እንዳሉ በአሳተሙት መርሐ አዝማን በተባለው የቁጥር መጽሐፍ በገጽ 138 ላይ ተገል ጿል። ለመሆኑ በቤተ ክርስቲያናችን አቆጣጠር ነው ? ወይስ በሳይንቲስቶች ነው ? ብለዋል ። መልሱ ካህን ባሕረ ሐሳብን ያወቀ ይሁን ብየ ትንተናውን በአጭሩ አቀርባለሁ ። ሳይንቲስቶች ተግተው በመሥራትና ሥራቸውም ለጠቅላላ ሕዝብ ጥቅምና አገልግሎት እንዲውል በየጊዜው እያሻሻሉና እያሣመሩ በማቅረባቸው ነው እንጂ ከሱባኤ ነቢያትና ከቀመረ ሊቃውንት መሠረትነት የወጣ አይደለም ። ከዚህ ቀጥዬ የሱባኤ ነብያት የቀመረ ሊቃውንት ውሳኔ ቤተ ክርስቲያን ያቆየችውን አቆጣጠር አቀርባለሁ ። 1ኛ ሱባኤ ነቢያትና ቀመረ ሊቃውንት መነሻው ንኡስ ቀመር ነው ። የተመሠረተበትም ምክንያት ከመሥራት ይፈልቃል ዕውቀት የተባለውን መጽሐፍ ከክፍል 6 እስከ 10 ድረስ መመልከት ነው ። ንኡስ ቀመር የቁጥሩ መደብ 19 ዓመት ነው ። ይህም በጠቅላላ በቤተ ክርስቲያን ካህናት ዘንድ አልቦ አበቅቴ በመባል የታወቀ መመሪያ ነው ። በዚህም መሠረት 4 ጊዜ 19 76 ዓመት ይሆናል ። ይህም 1 ማዕከላዊ ቀመር ይባላል ። 2ኛ 7 ጊዜ 19 133 ዓመት ይሆናል ። ይህም 1 ሱባኤ ቀመረ ነቢያት ይባላል ። 3ኛ 28 ጊዜ 19 532 ዓመት ይሆናል ። ይህም 1 ዓቢይ ቀመር ይባላል ። እነዚህ ሦስቱ፡ ዓበይት መምርያዎች በንኡስ ቀመር መደብ እየተመዘኑ ሁልጊዜ በዓመት በዓመቱ የሚነገሩና የሚቆጠሩ ናቸው ። ከእነዚህም ውስጥ 7 ማዕከላዊ ቀመር 1 ዓቢይ ቀመር ነው ።

እንዲሁም 4 ሱባኤ ቀመረ ነቢያት 1 ዓቢይ ቀመር መሆኑም መታወቅ አለበት ። በ2ኛው ክፍል ደግሞ በዓውደ ፀሐይና በዓውደ ኢዮቤልዩ ይቆጠራል፤ ይህም 1ኛ ዓውደ ሀሐይ 4 ጊዜ 7 28 ዓመት ይሆናል ። ይህም 1 ዓውደ ፀሐይ ይባላል ። 2ኛ ዓውደ ኢዮቤልዩ 5 ጊዜ 10 50 ዓመት ይሆናል ይህም 1 ዓውደ ኢዮቤልዩ ይባላል ። ይህ አጠቃላይ ቁጥር የሱባኤ ነቢያትና የቀመረ ሊቃውንት ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን የነበረ ያለ የሚኖር የቁጥር መመሪያ ነው የእነዚህም ዓበይት የቁጥር መደቦች በየአንዳንዳቸው ውጤት የሚከተለው ነው ። ከላይ እንደገለጽነው 7 ሺህ 472 ዘመን በንኡስ ቀመር ብቻ ሲመደብ 393 ንኡስ ቀመር ሆኖ 5 ዓመት ይቀራል ።ይህም ከ7467 ላይ ነው የቆመውና አስተውሉ ።

2ኛ/ በማዕከላዊ ቀመር 7ሺህ 448 ዘመን ሲመደብ 98 ማዕከላዊ ቀመር ሁኖ 24 ዓመት ይቀራል ። 3ኛ/ በሱባኤ ነቢያት ሲመደብ 56 ዓውደ ሱባኤ ነቢያት ሁኖ 24 ዓመት ይቀራል ። 4ኛ/በዓቢይ ቀመር ሲመደብ 14 ዓቢይ ቀመር ሁኖ 24 ዓመት ይቀራል 5ኛ በዓውደ ፀሐይ ሲመደብ 266 ዓውደ ፀሐይ ይሆናል ። 6ኛ በዓውደ ኢዮቤልዩ 249 ዓውደ ኢዮቤልዩ ይሆናል ።

በቤተ ክርስቲያናችን በሱባኤ ነቢያትና በቀመረ ሊቃውንት የሚቆጠረው ይህ ብቻ ነው ። ዝርዝር ሁኔታውን ሁሉ መርሐ አዝማንን ተመልከታችሁ ተረዱ ። በአጭሩ ከዚህ በላይ እንዳየነው 4 መቶ ስንኳ የሞላ የለምና አትሊያዩ ። በአባ ተክለ ድንግል የሐሳብ አቀራረብ ሱባኤ ነቢያትና ቀመረ ሊቃውንት ስምንት ሺህ እስኪሞላ ድረስ ምን ያህል ዘመናት እንዳለ በዚሁ በቀረበው የዝርዝር ሁኔታ መረዳት ነው ። እኔም እስከ 2ሺህ 642 ዓመት ድረስ ጽፌ የተውኩት የእኔ ሐሳብ የቆመበት ነው እንጂ የዘመን መጨረሻ ነው ማለቴ አይደለም እስከ ብዙ ሺህ ዘመን ልትቆጥሩ ትችላላችሁ ። ግን የራሳችንን ድርሻ በሰላምና በፍቅር በኅብረት ተስማምተን እንድናስልፍ ነው የሚገባን እንጅ የዘመኑ ብዛት የእኛ አይደለም ። ሆኖም በየቦታው ተስፋ ቆርጠው የተቀመጡ ሊቃውንት አሉና ጠይቋቸው ያስረዷችኋል ። ሰላም ለሰው ልጅ ሁሉ ይሁን።

መምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት

★★★

ተክሊል ያለ ቁርባን መፈጸም እንደማይገባው የቀደሙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወይም ሊቃውንት ያስተምሩ ነበር ። ዛሬ ግን በቤተ ክርስቲያናችን ተክሊል ያለቁርባን ሲፈጸም መታየቱ፡ ምሥጢር አይደለም ታዲያ ይህ ድርጊት ለምን ይፈጸማል ?

ተማሪ ሥፍራው አበበ
አዲስ አበባ

● ተማሪ ሥፍራው አበበ ስለጥያቄህ እናመሰግንሀለን ። ተክሊል ያለ ቁርባን እንደሚፈጸም በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የለም ። እርግጥ አንተ እንደተመለከትኸው በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያን ተክሊል ያለ ቁ

ወደ ገጽ ፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርዕሰ አንቀጽ

# ጌታችን ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ ለማን ታየ?

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ብዙ ጊዜ ለብዙ ሰዎች ታይቶአል ። ግን በግልጥ የታየባቸው ጊዜያት ዐሥራ አንድ ናቸው ፤እነዚህም እንደሚከተሉት ናቸው

1. ለማርያም መግደላዊት ማር.16 ፥ 9 ፡ ዮሐ 20 ፥ 15-16 (በኢየሩሳሌም)
2. መቃብሩን ጐብኝተው ለተመለሱ ቅዱሳት አንስት ማቴ 28 ፥ 9-10 (በኢየሩሳሌም)
3. ወደ ኤማሁስ ይሄዱ ለነበሩ ሁለት ደቀ መዛሙርት በመንገድ ታያቸው ሉቃ 24 ፥ 13 (በየሩሳሌም)
4. ለጴጥሮስ ብቻ ሉቃ 24 ፥ 34 (በየሩሳሌም)
5. ቶማስ ሳይኖር ለዐሥሩ ደቀ መዛሙርት ብቻ ታየ ዮሐ 20 ፥ 19 (በኢየሩሳሌም)
6. እንደገና ቶማስ ባለበት ከስምንት ቀን በኋላ ለዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ተገልጦአል ዮሐ 20 ፥ 26 (በገሊላ)
7. በገሊላ ባሕር በጥብርያዶስ አጠገብ ለሰባቱ ደቀ መዛሙርት ታይቶአል
8. በደብረ ገሊላ ለደቀ መዛሙርት ሁሉ ተገለጠ ማቴ. 28 ፥ 16
9. ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ጠቀሰው ለ500ወንድሞች ታይቷል 1 ቆሮ 15 ፥ 6 ።ግን አንዳንድ ሊቃውንት ይህን መታየት በደብረ ገሊላ የተደረገ መታየት እንደሆነ ይገምታሉ ።
10. ለያዕቆብ ብቻ አንድ ጊዜ እንደ ተገለጠ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15 ፥ 7 ተናግሮአል ። (በኢየሩሳሌም )
11. በ40ኛው ቀን በሚያርግበት ጊዜ ለደቀ መዛሙርት ሁሉ በቢታንያ ታይቷል ማር 16 ፥ 19-20 ። ሉቃ 24፥50-53 ።

መድኃኒታችን ክርስቶስ በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ለደቀ መዛሙርቱ በተገለጠ ጊዜ ብዙ ትምህርት አስተምሮአል ብዙ ተአምራት አድርጎአል ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ተመግቦአል፣ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸውና ለዘላለም ከእነርሱ ጋር እንደሚኖር ተስፋ ሰጥቶአቸዋል ይህ ሁሉ በእውነት ሞትን ድል አድርጎ የመነሣቱ ማረጋገጫ ነው ።ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ የታያቸው ሰዎች ሁሉ ክርስቶስ በእውነት እንደ ተነሳ በእውነት መስክረዋል ። ምስክርነታቸውም እውነት ነው ።ምስክርነታቸውን የሰዎች ዛቻ አልለወጠውም ፤ ሰይፍም አላስተባበላቸውም በእውነት የተነሣውን ክርስቶስ በግልጥ አይተውታልና ። -



# አሥራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል

ሕማማተ መስቀል እየተባሉ የሚጠሩት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጅ በደልና ኃጢአት የተቀበላቸው ጸዋትወ መከራ ናቸው ። ይህም ስለተባለ መድኃኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጅ የተቀበላቸው ጽዋትወ መከራ በቁጥር የሚወሰኑ ሆነው አይደለም ።



መድኃኒታችን መስቀሉን ተሸክሞ ሲሄድ እንደ ወደቀ

አንዳንድ ሊቃውንት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማተ መስቀል (በሦስት መቶ አሥራ ስምንት) በ318 ቁጥር ወስነው ተናግረዋል ሌሎች ደግሞ (ስድስት ሽህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት (6666) ናቸው ብለው በመወሰን ጽፈዋል አንዳንዶቹግን በክርስቶስ ላይ የተፈጸመውን ሕማም በቁጥር ወስኖ መናገር የዝናምን ጠብታ በጽሑፍ እሰፍራለሁ ብሎ ወረቀትና ብርዕ ይዞ እንደ መሰለፍ የሚያስቆጥር ሞኝነት ነው ይላሉ ።

ያም ሆነ ይህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ ለማሳሰብ ያህል እንጂ ሌላ ዓላማ በዚህ ጽሑፍ ለመጠቆም አልፈለግንም ስለዚህ የክርስቶስን ሕማማተ መስቀል ለማስታወስ እንችል ዘንድ በሊቃውንት ተጠንተው በጽሑፍ ተመዝግበው የምናገኛቸውን ዐበይት አሥራ ሦስት ሕማማተ መስቀል ቀጥለን እንመልከታቸው።

1ኛ ተአሥሮተ ድኅረት
2ኛ ተስሕቦ በሐብል
3ኛ ወዲቅ ውስተ ምድር
4ኛ ተዐርቆተ ልብስ
5ኛ ወሪቀ ምራቅ
6ኛ ተጸፍዖ መልታሕት
7ኛ ተቀስፎ ዘባን
8ኛ ተኮርዖ ርእስ
9ኛ አክሊለ ሦክ
10ኛ ፀዊረ መስቀል
11ኛ ተቀንዎ በቅንዋት
12ኛ ተሰቅሎ በዕፅ
13ኛ ሰሪበ ሐሞት

ጌታችን መድኃኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀል ከተቀበለ በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ተጠማሁ አለ አይሁድም እነሆ ተጠማሁ አለ ምን እንስጠው? የኖረ መጻጻ አምጥተን እንስጠው ተባባሉና አይሁድ ሊሞቱ ሲሉ ጣረሞት እንዳይበዛባቸው የሚጠጡትን ሆምጣጤ አምጥተው ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዳለ አቀመሱት እርሱም ሆምጣጣውን ከተቀበለ በኋላ ሁሉ ተፈጸመ በማለት ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለይቷል ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማመተ መስቀል በጠቅላላው "ሁሉ ተፈጸመ " ባለ ጊዜ አብቅቷል ። ክርስቶስ የተቀበላቸው ፀዋትወ መከራ ስለ እኛ ደኅንነት የተፈጸሙ ናቸው እነዚህን ሁሉ መከራዎች በደለኞች እኛ ልንቀበላቸው በተገባን ነበር ። ግን ክርስቶስ በእኛ ፋንታ ይህን መከራ ተቀበለ በእርሱም መከራ የእኛ የዘለዓለም ሕይወት ታደሰ ።

ቄስ ልሳነወርቅ በዛብህ

# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ርባን ይፈጸማል ። ይህም ወጣቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመጡ በኋላ ከመመለስ ይልቅ ለጊዜው በመቀበል ማስተማር የሚገባ መሆኑን በማመን ነው ። እዚህ ላይ ልንደብቀው የማንችለው ነገር አለ ይኸውም ለቤተ ሰብ እማካሪ የሆነው ካህን ከመጀመሪያ ጀምሮ ቢያስተምርና ቢመክር ኖሮ ይህ ድርጊት ባልተፈጸመም ነበር እስተማሪም ካለመኖሩ የተነሣ አንዳንድ ሙሽሮች በገዳም ውስጥ ተክሊል ለማስፈጸም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሄዱ የዓይን ምስክሮች አረጋግጠዋል ። የደብሩ አስተዳዳሪም "እኔ በእናንተ አልፈርድም ይህ ሁሉ የእኛ ስንፍና ነው" ብለዋል ። ወደፊትም ካህናት በትጋት እንዲያስተምሩ በዚህ አጋጣሚ መልእክታችንን እናስተላልፋለን ከዚህም ሌላ ወንድና ሴት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ የንስሐ አባታችሁ ማን ነው? ሲባሉ በመንገድ ጠምጥሞ ያገኙትን ሰው ጠርተው ይህ ነው አባታችን ብለው ሲያቀርቡ ተክሊሉን ፈጻሚው ክፍል በጥብቅ መቆጣጠር ይኖርበታል ምክንያቱም ይህ የመንደር ቄስ መሳይ ሰው ለጊዜው በገንዘብ የተገዛ እንጂ ለምእመናን አስተማሪ አይደለምና ።

★★★

በመጀመሪያ መንፈሳዊ ሰላምታዬን እያቀረብኩ ችግሬን በመዘርዘር ምክራዊ መፍትሔ ይሰጡኝ ዘንድ በመተማመን ነው ይኸውም እኔ ሁለቱ እግሬ ከቀን በኋላ ሽባ የሆንኩ በየጊዜው በመበሳጨት የልዩ ልዩ እፅዋት እና የባእድ አምልኮ እስረኛ ሆኛለሁ ።

ስለዚህ ከዚህ ሁሉ ጣጣ የምድንበትን መፍትሔ በዓምዳችሁ ላይ ምክራችሁን እንደምትለግሱኝ በመተማመን ነው ።

2ኛ/ ይህንን መጽሔት የአመቱን ክፍያ በማጠናቀቅ ከፍለው በፖስታ ቤት በኩል እንዲደርሳቸው ያደረጉ ግለሰቦ



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖረዋል ?

እጁጉ ረታ

እያንዳንዳቸው የሰውነታችን ውስጣዊ የአካል ክፍሎች ፣ በተፈጥሮአቸው ለየራሳቸው የሚያከናውኗቸው እጅግ አስደናቂ ተግባሮች አሏቸው ። ተግባሮቻቸውም ባጠቃላይ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላሉ

ሀ/ የምግብ ማዋሐድ ፣ የደም ማመላለስና የእስትንፋስ ፣

ለ/ በሽታን የመከላከል ፣ የማጥቃትና የማውደም ፣

እንደ ሥጋ እንደ ቅቤ ፣ እንደ እንቁላልና እንደ ወተት የመሳሰሉትን ከባድ ምግቦች በምንመገብበት ጊዜ ከ"ሀ" ተራ የተመለከቱትን ተግባሮች የሚያከናውኑት ሕዋሳቶቻቸው እጅግ ሥራ ስለ ሚበዛባቸውና ፣ ስለሚከብዳቸው ፣ በ"ለ" ክፍል የተመለከቱትን ተግባሮች በሚገባ ሥራዬ ብለው ለማከናወን አቅም ያንሳቸዋል ፣ ፋታም ያጣሉ ። በአንጻሩም ይህን ምናምኔውን ፣ አሸር ባሸሩን ፣ ቀጠላ ቅጠሉን በምንመገብበት ወቅት ሥራው ከሚቀላቸውም በላይ በሰውነታችን ውስጥ ለጤንነታችን ጠንቅ በሆኑት በሽታዎች ላይ ለማተኮር የተሻለ ዕድል ያገኛሉ ።

በተለይም ምንም ዓይነት ምግብ ባለመውሰድ ለተወሰነ ጊዜ የምንቆይ (ማለት የምንጾም) ከሆነ ፣ እኒህ ሕዋሳቶቻችን በሽታን ለመከላከል፣ለማጥቃትና ለማውደም ከዚህም በላይ ለጤንነታችን የሚያስፈልገውን ማናቸውንም እንክብካቤ ለማድረግ የሚያስችል የሰከነ ጊዜ ወይም ዕረፍት እንዲያገኙ አመቺ ሁናቴን ፈጠርንላቸው ማለት ነው ። በዚህም በቤተ ክርስቲያናችን የታዘዙት አጽዋማት በሚገባ ከተጠበቁ የሚጫወቱት ከፍ ያለ ሚና እንዳለ ለመረዳት እንችላለን ። ይህም ማለት መንፈሳዊ ሕይወታችንን ለመገንባት በተወሰኑ ወቅቶች የምንጾማቸው አጽዋማት እግረ መንገዳቸውን ለአካል ጤንነት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደ መግደል ያህል ነው ።

እዚህ ላይ እያንዳንዳቸው የሰውነታችን ውስጣዊ ክፍሎች ጤንነታችንን በመንከባከብ ረገድ የሚያከናውኗቸው ተግባሮች እጅግ አስደናቂ ስለሆኑ ልናውቃቸው ይገባል ።

ስለዚህ በዛሬው ዝግጅት የኩላሊትን ተግባር ባጭሩ ለማቅረብ እ[illegible]ራለሁ። ኩላሊት ሲመለ[illegible] ንድ ትንሽ ሞለል ያለ ድብልቅልቅ ያለ ነገር ነው። ይሁን እንጂ ኒፎሮንስ በተባሉ ቀጭን ቱቦ መሰል ጥቃቅን ማጣሪያዎች (ፊልተርስ) አማካይነቱ የሚያከናውናቸው ተግባሮች እጅግ በጣም የሚያስደንቅ ሆኖ ይገኛል ። እኒህ ኒፎሮንስ በሚባል ስም የታወቁት ጥቃቅን ነገሮች እንደ ቀጭን የላስቲክ ቱቦ ውስጠ ክፍት ሲሆኑ ቁጥራቸውም እስከ ሁለት ሚሊዮን ተኩል እንደሚደርስ ተገምቷል ። እያንዳንዳቸውም በመስመር ሆነው ቢቀጣጠሉ ወደ ሰማኒያ ኪሎሜትር ርዝመት ሊጠጋ የሚችል ቁመት እንደሚወጣቸው ታውቋል ።

ምናልባትም ከአንጐል ቀጥሎ እጅግ የተወሳሰበ ተግባር ከሚያከናውኑት የውስጥ አካላችን ክፍሎች ሁለተኛውን ደረጃ የሚይዘው ኩላሊት ሳይሆን እንደማይቀር ይታሰባል ።

እንግዲህ ጾም በምንጾምበት ጊዜ የምግብ ማዋሐጃ የደም መመላለሻና የመተንፈሻ ሕዋሳት እረፍት ላይ ስለሚሆኑ ፣ ኩላሊት ኒፍሮንስ ከተባሉት ማጣሪያዎች አማካይነት ከሳምባና ከጉበት ጋር ግንባር ፈጥሮ ፣ ልዩ ልዩ ጣፋጭና ከባድ ምግቦችን ከመመገባችን የተነሳ በሰውነታችን ውስጥ የተጠራቀሙትን መርዛማ ነገሮች እያጣራ ወደ ውጭ ያስወግዳቸዋል ። ባጠቃላይ የጾም ጠቃሚነቱ ለነፍሳችን ብቻ ሳይሆን ለጤንነታችንም ጭምር መሆኑን አውቀን ፣ ከጥሉላት ምግብ ብቻ ሳይሆን ከማናቸውም የሚበላ ነገር ሁሉ ለተወሰነ ጊዜ ብንቆጠብ ራሱ ሰውነታችን የሚያመጣውን ለውጥ ለመረዳት እንችላለን ።

# ደብዳቤዎች

ች አሉ ከዚህም አንዱ ወንድሜ ሲሆን እኔም ከእሱ እየተዋስኩ አነብ ነበር ነገር ግን ከመስከረም ወር 72 ዓ.ም. ጀምሮ በወቅቱ ባለ መድረሱ በማህበርተኞቹ ላይ ቅሬታ ተፈጥሮአል ይህ የሆነው ከእናንተ ነው ወይንስ ከላኪው ፖስታ ቤት መልሳችሁን እጠባበቃለሁ ።

● አቶ ታምራት መንክር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በደረሰብዎ ሕመም ምክንያት በመበሳጨት የዕፅዋትና የባዕድ አምልኮ እስረኛ መሆን ከሕመም ሊፈውስዎ አይችልም ። በዚህ ፋንታ በትእግሥት ሆነው 1ኛ በሕክምና 2ኛ በጸሎት ና በጠበል ለመጠቀም ቢሞክሩ እጅግ መልካም ነው ። ከዚህ በቀር የሚያድንዎ ሌላ ነገር ያለ አይመስለኝም ። ዕፅዋትን መቆርጥም ማጨስና መጠጣት በአካልም ላይ ሌላ ጉዳትን ያስከትልብዎታልና እንዲተው እመክርዎታለሁ።አምልኮተ ባዕድ ወደሚፈጸምባቸው ቦታዎች በመሄድ ተስፋ ቢስ የሆኑ የጠንቋይ ቃላትን መስማት ስጋትን ጭንቀትንና ትካዜን ያሳድርብዎታል እንጂ አይጠቅመዎም ።

ሁለተኛ የመጽሔታችን በጊዜው አለመድረስ በእኛ ስሕተት አይደለም ። መጽሔቱ ምንጊዜም ቢሆን ከማተሚያ ቤት እንደወጣ ለደንበኞቻችን በየአድራሻቸው እንልካለን ይሁን እንጂ በትክክል ለደንበኞቹ የማይደርሰው በወቅቱ ወደ ፖስታ ቤት ባለመሄዳቸው የመጽሔቶቻቸውን ደንበኞች በየወሩ መጀመሪያ በአድራሻቸው ቢጠባበቁ ወይም የራሳቸውን ሰው ቢወክሉና በሚገባ ሊደርሳቸው የሚችልበትን አድ

ወደ ገጽ ፮ ዞሯል



# ሊቃውንቶቻችን

## ብፁዕ አቡነ ሚካኤል

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ግፈኛው የኢጣልያ ፋሽስት ኢትዮጵያን በዕብሪትና በግፍዕ በወረራት ጊዜ እንደ ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት እንደ አቡነ ጴጥሮስ ስለሀገራቸው ነፃነትና ክብር በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር በጠላት ተደብድበው የሞቱት የብፁዕ አቡነ ሚካኤል የሕይወት ታሪክና ዜና ሞት እንደ እነ አቡነ ጴጥሮስ በጋዜጦችም ሆነ በመጽሔቶች እንዲሁም በልዩ ልዩ የታሪክ መጻሕፍት በይፋ ሳይገለጽ መቆየቱ ብዙዎችን እንዳሳዘናቸው ግልጽ ነው ።

ለሁሉም ጊዜ አለውና የብፁዕነታቸው የሕይወትና የዕረፍት ዜና በዚህ መጽሔት በአሁኑ ጊዜ ሊገለጽ ችሏል ።

### የሀገረ ሙላዳቸውና የትውልዳቸው ዜና

የጵጵስናን ሥልጣን ከመቀበላቸው በፊት ኀይለ ሚካኤል ተብለው ይጠሩ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በጐንደር ክፍለ ሀገር በአፈረዋናት ልዔ መስቀለ ክርስቶስ በተባለ ቦታ ተወለዱ ።

በዚያው በተወለዱበትም አካባቢ ግንድ አጠመም ቅዱስ ሚካኤል ከተባለ ቤተ ክርስቲያን ክርስትና ሲነሡ ስመ ጥምቀታቸው ኀይለ ሚካኤል ተባለ ።

### ትምህርት

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በትውልድ አገራቸው መሪ ጌታ ዋሴ ከተባሉ አስተማሪ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ገላውዴዎስ መሪ ጌታ ተድላ ከሚባሉ አስተማሪ ፀዋትወ ዜማ ማኅደረ ማርያም ከመምህር ወልደ ሩፋኤል መዝገብ ድጓ ተማሩ ከግብፃዊው አቡነ ጴጥሮስም ሢመተ ዲቁና ተቀብለው በዚያው በትውልድ አገራቸው ዘገቦ ጽዮን በተባለ ቤተ መቅደስ በዲቁና አገልግለዋል ትምህርታቸውን ለማሟላት በነበራቸው ፍላጐትም ወደ ጐንደር ከተማ ሔደው የብሉያትንና ሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ አድርገው አጠኑ የብሉያትም ትርጓሜ መምህራቸው መምህር ተስፋዬ ናቸው ።

ከዚህም በኋላ ወደቦሩ ሜዳ ከመምህር አካለ ወልድ ዘንድ ሔደው የሐዲሳትን ትርጓሜና ስልት በድጋሚ አጠናክረውና ቅኔያቸውን አስፋፍተው ለቅኔ መምህርነት ተመረቁ ።

ቀጥሎም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር የአሥራ አራቱን ቅዳሴያት ዜማ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ተምረዋል ፣ የቅስና ሥልጣንም ከግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ ተቀብለዋል ።

በትምህርትና በመልካም ጠባይም ተመርጠው የወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ አበነፍስ ሆነዋል የሞያና የግብረ ገብነት ተቀዋማቸውም ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከረ መሔዱ በብዙዎች ስለታወቀ በቤተ መንግሥቱ በኩል በምክር እንዲረዱ ተደረገ ፣ ወዲያውም መጀመሪያ የዜና ማርቆስና የዝቋላ ገዳማት አስተዳዳሪነት ተሰጣቸው ።

በኋላም የአዲስ አበባ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል እልቅና ከተሰጣቸው በኋላ በተከታታይ ደግሞ የማኅደረ ማርያምን እልቅና ተሾመው ነበር ከሹመት ወደ ሹመት በተዛወሩበት ወቅት ሁሉ ትምህርት በመስጠትና ምእመናንና ካህናትን በማስተባበር ረገድ ያሳዩት ተግባራዊ ውጤት ለሊቅነት ይዞታቸው ታላቅ መከሰቻ ሆኗል ።

### ጵጵስና

በኮፕትና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነበረው የጵጵስና ሹመት ክርክር ተፈጽሞ ኢትዮጵያውያን ወደ ጵጵስና ሹመት መድረክ እንዲቀርቡ ሲደረግ በሊቅነት ሞያቸው በትምህርትና በመንፈሳዊ አገልግሎት አስተዋፅኦዋቸው ቀደም ብለው የታወቁት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የጵጵስና ሹመት እንዲሰጣቸው ከተመረጡት ከነብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና ከነአቡነ አብርሃም የምርጫ ዕድል ደርሷቸው በ1921 በእስክንድርያው ፓትርያርክ ሢመተ ጵጵስና ተቀበሉ በዚህም ጊዜ ኀይለ ሚካኤል የነበረው ስማቸው ቀርቶ ሚካኤል ተብለው እንዲጠሩ ሀገረ ስብከታቸውም የኢሉባቡር ክፍለ ሀገር እንዲሆን ተደረገ ።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከ1921 ዓ.ም.እስከ 1928 ዓ.ም.ድረስ ለስምንት ዓመት የሀገረ ስብከታቸውን ምእመናንና ካህናት በመንፈሳዊ ትምህርትና ምክር ሲያጠናክሩ ተወዳጅ የነበረውንም ሐዋርያዊ ተልዕኮዋቸውን ሲያፋጥኑ ከቆዩ በኋላ በ1928 ዓ.ም ግፈኛው ኢጣልያ ፋሽስት ኢትዮጵያን በግፍዕ ስለወረራት ብፁዕነታቸው የፍጹም አባትነት ስሜትና ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ ናት እንጂ የሌላ አይደለችም በማለት የሀገር ፍቅር ነበራቸው ።

በቆራጥነትና በጀግንነት ወኔ እየተቀሰቀሱ በድፍረት የሚሰጡትም ትምህርት የኢጣልያን ፋሽስት የግፍ ወራሪነትና ኢትዮጵያውያንን እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ አድርጐ በጠላታቸው በኢጣልያ ፋሽስት ላይ የኀብረት ክንድን እንዲያነሡና የኢትዮጵያን ነፃነት በአፋጣኝ እንዲመልሱ የሚቀሰቅስና የኀብረት ትጥቅ የሚያስታጥቅ ሆነ ።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በሙሉ የሐዋርያነት ስሜት ለሕዝብ የሚያስተላልፉት ስብከት የሚጐዳው መሆኑን ግፈኛው ጠላት በቅርቡ ተከታትሎ ካወቀ በኋላ በኢትዮጵያ ላይ የነበረውን የበላይነት ዐወቀው በዚሁ ፈለግ ሕዝቡን እንዲያስተባብሩና እንዲሰብኩለት በመልእክትም በደብዳቤም ላቀረበላቸው ጥያቄ ከእውነተኛው የሀገር ፍቅር ዓላማ እንደማያፈገፍጉ እስከ መጨረሻቸውም ደማቸውን አፍስሰው ለውድ አገራቸው ቤዛ ለመሆን የማይቀዘቅዝ ስሜት እንዳላቸው በሙሉ ልብ ስለአረጋገጡ በሌሎች ሀገር ወዳዶች ኢትዮጵያውያን ላይ እንደፈጸመው በግፍ እንዲደበደቡ ከማድረግ በቀር ሌላ ምርጫ አለመኖሩን በትክክል ተገነዘበ ።

### ዕረፍታቸው

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንዳቸውን በጠላት ላይ እንዲያነሱ ከአውራጃዎች ወደ ወረዳዎች እየተዘዋወሩ ውግዘት ጭምር የሚያስተላልፉትን ቃለ ስብከት በመቀጠል በጉዞ ላይ እንዳሉ ሰቢ ከሚባል ሜካ ውስጥ በጠላት ጦር ተከበው በቈራጥነትና በአርበኝነት ሲዋጉ አንድ ሌሊት ካደሩ በኋላ በጠላት ተይዘው ለጥያቄ ቀረቡ ።

ለቀረበላቸውም ጥያቄ ግፈኛውን ፋሽስት በኢትዮጵያ የበላይነት ወይም አስተዳዳሪነት መደብ በፍጹም የማያውቁትና ኢት

ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ሰባቱ ነገራተ መስቀል

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ድኅንነት በሰው ባሕርይ ተገለጠ በዓለም በሰዎች መካከል ተመላለሰ ፤ ዓለም ከጥፋት ይድን ዘንድ ዓሉ የሚድንበትን ሁሉ ሥራ አስተማረም ዓለም የሚድነውም በአንድ በራሱ በእግዚአብሔር ልጅ መሥዋዕትነት ነበረ፤ ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ እስከ አቀረበባት ዕለት ድረስ ብዙ ሠርቶ እል አስተምሯል ተናግሯልም ለምሳሌ ባጭሩ ከመስቀል አስቀድሞ አርባ ቀን ጾመ ፤ በጾሙም ወቅት የተፈታተነውን ሰይጣን ድል ነሣ እርሱ በሦስት ነገሮች ማለት በስስት በትዕቢትና በፍቅረ ንዋይ ድል የነሣውን ሰዎች ድል እንዲነሡት እርሱ ድል ነሣ ከዚህ በኋላ ለሦስት ዓመታት ተኩል ያህል በየመንደሩና በየከተማው እየተዘዋወረ አምላክነቱን የሚገልጽ ብዙ ሥራ ውሃውን የወይን ጠጅ አደረገ ፤ በደረቅ (በልሙጽ) ግንባር ዓይን ፈጠረ በውሃ ላይ ሄደ ሙት አስነሣ ድውይ ፈወሰ ፤ በአምስት እንጀራና በጥቂት ዓሣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን አጠገበ ወዘተ ይህ ሁሉ ከቅድስት ድንግል ነፍስንና ሥጋን የተዋሐደው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን የሚያስረዳ ነው ።

ከዚህ በኋላ ስለ ዓለም ድኅንነት ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ባቀረበበት ወቅት በመስቀል ላይ ሰባት ዓበይት ነገሮችን ተናግሯል እነርሱም የሚከተሉት ናቸው 1ኛ "የሚያደርጉትን አያውቁምና አባት ሆይ ይቅር በላቸው" በማለት ለሰቀሉት በጦር ለወጉት በምስማር ለቸነከሩትና ምራቃቸውን ለተፉበት የጸለየው ጸሎት ነው "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" የሚለውን ስንመለከት የማያውቁት ምኑን ነበር ? አድራጎታቸው የማይገባ መሆኑን ? ወይስ ክርስቶስ በደል የሌለበት መሆኑን ? ብለን እናስ ባለን አዎ ሰዎቹ ክርስቶስ ምንም ዓይነት በደል የሌለበት ንጹሕ አምላክ መሆኑን ያውቁ ነበር ነገር ግን በደል የሌለበትን ክርስቶስን በመስቀላቸውና በመግደላቸው በራሳቸውና በአገራቸው ላይ ምን አይነት ፍርድ እንደሚመጣባቸው አያውቁም ነበር ። ስለዚህም በትንቢተ ኢሳይያስ 53፥12 ላይ "እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ" ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ለዓመፀኞቹ ጸለየ ።

2ኛ "አምላኬ ሆይ ለምን ተውኸኝ" በማለት የተናገረው ነው ፤ ለምን ተውኸኝ ማለቱ ክርስቶስ ራሱ ከባሕርይ አባቱ የተለየና ያነሰ ሆኖ አይደለም" ለምን ተውኸኝ" ብሎ መጸለዩ ግን ስለራሱ ሳይሆን ራሱን የሠመረ መሥዋዕት አድርጎ ስላቀረበላቸው ስለምእመናን ነው ፤ ምእመናንን በደሙ ስለዋጃቸው ለምእመናን የጸለየው ጸሎት መሆኑን ለመረዳት በዮሐ. 17፥11 "ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ ጠብቃቸው" ያለውን ማስተዋል ነው ፤ ከዚህም ሌላ በመዝሙረ ዳዊት 21፥1 "አምላኬ ለምን ተውኸኝ" የሚለው ትንቢት ስለ መሲሑ ስለ ክርስቶስ የተነገረ መሆኑን አይሁድ ያውቁ ነበርና መሲሕ ክርስቶስ ራሱ መሆኑንና ትንቢቱም መፈጸሙን ለማስረዳት ጭምር ነው ።

3ኛ "ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ" ሲል በእምነት ለጠየቀውና በቀኙ ተሰቅሎ ለነበረው ወንበዴ "ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ" በማለት የሰጠው የድኅንነት ቃል ነው።



መድኃኒታችን ክርስቶስ በ2 ወንበዴዎች መካከል እንደ ተሰቀለ

በግራው የተሰቀለው ወንበዴ "አንተ አምላክ ከሆንህ እኛንም ራስህንም አድን" በማለት ተገዳደረው በቀኝ በኩል የተሰቀለው ይህን ሰምቶ "አምላክህን እግዚአብሔርን አትፈራውም ? እኛ እንደሚገባ በሥራችን ተፈርዶብናል እርሱ ግን ምንም ዓይነት ክፉ ሥራ አልሠራም" በማለት ጓደኛውን ከገሠጸ በኋላ ወደ ክርስቶስ መለስ ብሎ "ጌታ ሆይ በጌትነትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ" በማለት የክርስቶስን አዳኝነትና ዳግመኛም ለፍርድ የሚመጣ መሆኑን አመነ ። ስለአመነም ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትኖራለህ ማለት በደስታ ከእኔ ጋር ትኖራለህ የሚል የድኅንነት ቃል ተሰጥቶት ድኗል ፤ በልዑልም ፊት በደስታ ይኖራል ።

4ኛ "እነሆ ልጅሽ እነሆዋት እናትህ" በማለት እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለሚወደው ደቀ መዝሙር ለዮሐንስ ዮሐንስንም ለእርስዋ አደራ በመስጠት እርስ በርሳቸው እንዲጠባበቁና እንዲረዳዱ በማድረግ ምዕመናን ለቅድስት ድንግል ማርያም ማርያምንም ለምዕመናን ሰጠ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱን በተለይ ለዮሐንስ አደራ የሰጠበት ምክንያት ዮሐንስ እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት በሰይፍ ወይም በስቅላት እንደማይሞትና ብዙ ዘመን እንደሚቆይ በአምላክነቱ ስለሚያውቅ ነበር ይህም ለእመቤታችን ከአንድ ልጅዋና ከደቀ መዛሙርቱ በቀር ምንም ዘመድና ረዳት እንዳልነበራት ያስረዳል ። ከዚህም ጋር "እነሆ ልጅሽ እነሆዋት እናትህ" ሲል በዮሐንስ አማካይነት ምእመናንን ለእመቤታችን የአደራ ልጆች እርስዋንም ለምእመናን የአደራ እናት አድርጎ መስጠቱ እንደሆነ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ያስተምራሉ በእርግጥም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለምእመናን ምሕረትን የምትለምን አማናዊት አማላጃችን እንደሆነች እናምናለን ። እናስተምራለን ።

5ኛ (ጸማዕኩ) (ተጠማሁ) ያለው ቃል ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ሰዓቱ ቀትር ሲሆን ከቀትርነቱም በላይ ቀኑ እጅግ ሞቃት ነበር ፤ በጦር ሲወጉትና በምስማር ሲቸነከሩት ብዙ ደም ፈሰሰው ስለዚህ "ተጠማሁ" አለ በዚህ ጊዜ ወሃቤ ማየ ሕይወት ለሆነው ክርስቶስ መጣጣ አጠጡት ፤ በዕርግጥ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ስለሆነ ከሙቀት ብዛትና ከደሙ መፍሰስ የተነሣ ውሃ ጥም አጥቅቶት አይደለም ግን "በመብሌ ሐሞት ጨመሩ ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ "መዝ. 68፥21) ተብሎ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ "ተጠማሁ" አለ ፤ ተጠማሁ ባይል ኖሮ ሆምጣጤውን ሊያጠጡት አይችሉም ነበርና ። ከዚህም የተነሣ ትንቢቱ አይፈጸምም ።

6ኛ "አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" ብሎ በራሱ ሥልጣን ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው የለየበት ቃል ነው ይህም የሰው ሁሉ ነፍስ ዘላለማዊትና ሕያዊት መሆንዋን ከማስገንዘቡም በላይ ሰው በሆነ ጊዜ ከእመቤታችን ሥጋና ነፍሴን የተዋሐደ መሆኑን ያስረዳል ።

7ኛ "ወይቤ ተፈጸመ ኩሉ ፤ ሁሉ ተፈጸመ" በማለት የተናገረው የመጨረሻ ቃል ነው ተፈጸመ የተባለውም ጌታችንንና መድኃኒታችን ክርስቶስ በዚህ ዓለም በሥጋ የኖረው ዕድሜ ነው 2ኛ የተመሰለው ምሳሌ የተነገረው ትንቢት ደረሰ ተፈጸመ ማለት ነው ቃለ እግዚአብሔር ወልድ የአዳምን ባሕርይ ባሕርይ እንደሚያደርግና በእርሱ ሞት አዳም ከነልጆቹ ደኅንነትን እንደሚያገኝ ምሳሌ ሲመሰል ትንቢት ሲነገር ኖሮ ነበርና "ሁሉ ተፈጸመ አለ" ከዚህም ሌላ ድኅነተ ዓለም ፍጹም ሆነ ዓለም በሙሉ በእኔ ዳነ ማለቱ እንደሆነ እናምናለን ፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ የተናገራቸው ሰባቱ ነገራተ መስቀል " የሚባሉት ከዚህ በላይ የተነገሩት ናቸው ምእመናን ሁሉ እነዚህን ቃላት ማወቅ እንደሚኖርባቸው ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ።

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፬ የዞረ

ራሻ ለድርጅታችን ማስታወቅ እንዳለባቸው በዚህ አጋጣሚ መልእክታችን እናስተላልፋለን ።

★★★

ከሁሉ አስቀድሜ ሥራችሁ እንዲቃናላችሁ የዘወትር ምኞቴ ነው ። አንዳንድ ሰዎች ጋብቻቸውን በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተክሊል ይፈጽማሉ ይህም እጅግ ያስደስታል ፤ ነገር ግን አንዳንዶቹ ሙሽሮች ከእነአጃቢዎቻቸው በአልኮል ተመርዘው ከቀኑ በ6 ወይም በ10 ሰዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት በተክሊል ሲጋቡ ይታያሉ ።

ጋብቻው በተክሊል መሆኑ በአልከፋም ነበር ። ግን በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው ሥርዐት ከስካር በኋላ መሆኑ ቤተ ክርስቲያን የምትፈጽመው ሥርዐት ነው ? በእኔ አመለካከት ስህተቱ የሙሽሮቹ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባለማስተማራቸው ምክንያት የሚሆን መስሎ ይታየኛል ።

ወ/አማኑኤል ዘለለው
አዲስ አበባ

● አቶ ወ/አማኑኤል ዘለለው የራስዎን ጥያቄ ራስዎ መልሰውታል ይኸውም የካህናት አለማስተማር ነው ያሉት ነው ግን ጉዳዩ የካህናት አለማስተማር ብቻ እንዲሆን አንገምትም ራሳቸው የሚጋቡትም እውነተኞች ክርስቲያኖች ከሆኑ አይሰክሩም ፤ ሰክረውም ወደ ቤተ ክርስቲያን አይመጡም ። ይህም የክርስትና ትምህርት ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ሞራል ነው ። ሆኖም ለክርስቲያን ሞራል ኃላፊነት ያላቸው ካህናት ስለሆኑ ምንጊዜም ቢሆን ካህናት የሰበካቸውን ምእመናን ስለጋብቻና ስለ አፈጻጸሙ ሁሉ መምከርና ማስተማር ይኖርባቸዋል።


www.ethiopianorthodox.org

# ዓለም አቀፍ የጥናት ጉባኤ

(ከቁጥር 29 የቀጠለ)

## ወደ አዲስ ክርስቲያናዊ የኅብረተሰብ ሞራልና የቤ ክ መምሪያ

በዚህ ርእስ ላይ ቡድን 10 በሰፊው ተወያይቶአል ።

ቡድን 10 ከ9 ቡድኖች የተወጣጡ ተወካዮች የሚገኙበት ሲሆን ኃላፊነቱም ከጉባዔውና ከቡድኑ ውይይት ሊያዝነው ታሪካዊ ዘመን የኅብረተሰብ ሞራልና ለቤ/ክርስቲያን መመሪያ ዕድገት ፍንጭን ለማግኘት ነው ቡድኑ ሌሎች ቡድኖች ያልመለሷቸው ጥያቄዎች ቢኖሩ ለመመለስና ለቤ ክ አዲስ የኅብረተሰብ ኢቴክስ (ግብረገብነት) ለመስጠት ሳይሆን በዓለማችን ውስጥ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በአሁኑ ጊዜ ማድረግ የሚገባቸውን ለመጠቆም ያህል ነው ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው የእግዚአብሔር ሥራ ፍቅር ነው ። ፍቅሩም ወሰን የሌለው እውነተኛ ነው ። የእግዚአብሔር ፍቅር መፈጸም የዓለም ሥራዋ ፣ መስቀሉም ምልክትዋ መሆን አለበት ። በመስቀሉ ላይ የእግዚአብሔር ኃይል መገለጥ ፣ የሰው ልጆችም ኃይል መወሰን ሆኗልና ። እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው ። ዓለምም ፍጥረቱ ነች ፣ እኛ ወንዶችና ሴቶችም እናደርገው ዘንድ እግዚአብሔር ያቀደውን የፍቅር ኑሮ መኖር አልቻልንም።ይሁንእንጂ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ፍቅር የኛን ጥፋት እንደሚያሸንፍ እንመሰክራለን።ስለዚህም ፍትሕ ፣ ሰላምና ደስታ ሁሉ የሚገኝባትን የእግዚአብሔርን የፍቅር መንግሥት መምጣት በአንድነትና በተስፋ እንጠባበቃለን ።

የማንም ሰብአዊ ተግባር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያናውጠውና ሊለውጠው አይችልም ። እኛ በርሱ መንፈስ የምንኖር ነን ። ታሪካዊ እውነታ በሆነው በኢየሱስ በተገለጠው የእግዚአብሔር ሥራ የተስፋ መሠረት አለን ። በመሆኑም ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር መንፈስ በመገፋፋት ለመሥራት እንነሣለን ። ሥራችንም ውሱን ቢሆን በፍቅር በአንድ ላይ ለመኖር ነውና ከፍተኛና እርግጠኛ ዕድል ነው ። ለዚህ ነው ለፍትሐዊ ሱታፌአዊና ህልውናው ለተጠበቀ ኅብረተሰብ ምሥረታ የምንነጋገረው ።

የባንጋሎሩን አነጋገር እንደሚከተለው ሲሆን በንግግሩ ጠቃሚ ቃሎችን ሠንዝሯል ። "እኛ የአለን የአሁኑ ተስፋ በታሪክ ከእግዚአብሔር ሥራ ጋር ፣ ከሚመጣውም ዘለዓለማዊ ሕይወት ጋ የተያያዘ ነው ። ... እኛ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ፍቆ እንደተቀበለን እናውቃለን ። ስለዚህም ወደ ሕጉቹ በማተኮር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለመሥራት እንደሚያስችለን እርግጠኞች ነን ። በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እናያለን ። ኢየሱስም እውነትንና ጽድቅን በመግለጥ ይመጣል ።

በዚህ ስብሰባ ስለፍትሐዊ ተሳትፎአዊና ህልውናው ስለተጠበቀ ህብረተሰብ እንዲሁም የዚህ ዓይነት ኅብረተሰብ ምን እንደሆነ ተነጋግረናል ። ለነዚህም ቃሎች ግለት ለትክክለኛ ፣ ሱታፌአዊ ኅብረተሰብ ትርጉም ለመስጠት እንሞክራለን ።

ፍትሐዊ ኅብረተሰብ፦ ግለሰቦችና ማኅበረሰቦች ለሁሉም ዕድገት ትብብር የሚያደርጉበት ነው ። ይህም ሰዎች እርስበርሳቸው በመገናኘት ለሁሉ ጥቅም የሚሠሩበት ነው ። ግጭት ሳይኖር ስምምነትን እንጠብቅም ። ግለሰቦች በኅብረተሰቡ ውስጥ ትርጉም አላቸው ። ከዚህም በላይ የሚመጣውን ተጽእና መቋቋም ይገባቸዋል ። አንዳንድ ኅብረተሰቦች በዓለም ኅብረተሰብ በአንዱ ላይ ይሠራሉ ። ከዚህ በላይ መሊያቸውን በመጠበቅ በሁላቸውም ላይ የሚሆነውን ተጽእኖና የሚካሄደውን ጭቆና መቃወም አለባቸው ። በዚህ ዓይነት ኅብረተሰብ ሰዎች በነፃነትና በኃላፊነት ሰው የመሆን ዕድል አላቸው ። ከባህልና ከማኅበራዊ ኑሮ ጋር አብሮ የሚሄድ ነውና እውነተኛ ሰብአዊ ሕይወት (ኑሮ) ምን ዓይነት እንደሆነ አጠቃላይ መግለጫ ለመስጠት እንሞክርም ። ይሁን እንጂ በማንኛውም ኅብረተሰብ ሰው ራሱን በራሱ በማሳሳት ምኞታዊ ፍላጎቶችን ሁሉ ወደ አስፈላጊ ነገሮች በማዞር ሌሎችን ሰዎች እንደሚጎዳ ሳናሳስብ አናልፍም ። ትክክለኛ ኅብረተሰብ ከጅምላ ፍላጎቶች ይልቅ በጣም አስፈላጊ ለሆኑ ለመሠረታዊ ፍላጎቶች ቅድሚያ ይሰጣል ።

ሱታፌአዊ ኅብረተሰብ፦ ውሳኔ በሚተላለፍበት ጊዜ ውሳኔው የሚነካቸው ሰዎች በትክክል የሚጠቃለሉበት ነው ። ውሳኔዎች የሚተላለፉት ለሕዝብ ብቻ ሳይሆን በሕዝብም ጭምር መሆኑን ያሳያል ። የተሳትፎው ሁኔታ ከአገር ወደአገር ከኅብረተሰብ ወደ ኅብረተሰብ ይለያይ እንጂ ፣ በየትም ቦታ ተሳትፎው ስለውሳኔ ማሳለፍ ብቻ ሳይሆን ስለተፈጥሮ ሀብት ፣ ስለ ማቴሪያልና መንፈሳዊ ስለሆኑ ጉዳዮችን እንዲሁም ሌሎችን የሚያጠቃልል ነው ። ፍትሕና ተሳትፎ በኅብረተሰቦችና በግለሰቦች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚያጎላና የሚያጠናክር ነው ።

ህልውናው የተጠበቀ ኅብረተሰብ፦ ለጥፋት ሳይሆን ለሕይወት ሕዝቡ አንዱ ከአንዱ ጋር የሚኖርበት ነው ። በአሁኑ ጊዜ ብዙው የዓለም ሕዝብ እንደተረዳው ሁሉ በወቅቱ የሚካሄደው የፍጆታ ልማድ ሰዎች የሚኖሩበትን የተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ አስግቶታል ። ሰው የኤኮሲስተም አባልና ከእግዚአብሔር ፍጥረቶች አንድ እንደመሆኑ መጠን በሚበጅ ሁኔታ ኑሮውን መግፋት አለበት ። ኤኮ ሲስተሙን በማጥፋት ላይ የሚገኙ ድርጊቶች ኅብረተሰቡንም ያጠፉታል ።

በዚህ ስብሰባ በመገኘት የኛ ታሪካዊ ሁኔታ የተለየ እንደሆነ እናስተውላለን ። የሰው ዘር እንደዚህ ያለ ኃላፊነት ፣ አደጋና ዕድል የኛ ትውልድ የገጠመውን ያህል ድር ገጥሞት አያውቅም ። በማዳን ወይንም በማጥፋት ኃይል ፣ በምድር ላይ ወይንም በአየር ላይ በአለው ግንኙነት ፣ አተሞችን በመከፋፈል ሆነ በሌሎች ላይ ሠልጥነናል ። ደግሞ ተበድለናል ። የብዙ ቴክኖሎጂ ኃይል አለቃዎችና ተገዥዎች ሆነናል ። አያቶቻችን ያላስተላለፉትን ውሳኔ የማስተላለፍ ግዴታ በላያችን እያንዣበበ ነው ። በታሪካዊ ድርጊቶች እግዚአብሔር በጸጋና በፍርድ ሰውን የተገናኘበትን የክርስትና እምነት ኃይል ያስማናል ። በታማኝና በሚታመን እግዚአብሔር ፍቅሩ በማይለወጥ አምላክ ፣ ነገር ግን አዲስ ነገሮችን በነፃነት እያደረገ ሰዎችንም አዲስ ነገር እንዲያደርጉ በነፃነት በሚጠራ በእግዚአብሔር እናምናለን ። ከተለያዩ ቦታዎች የተሰበሰብን ሰዎች የተለያዩ ማኅበራዊ ሁኔታዎች የቱን ያህል ልማዳችንን አስተሳሰባችንንና ሞራላችንን እንደለያዩት እናውቃለን ። አንዳንዶቻችን ሕይወታችንን በሳይንሳዊ ድርጅቶችም በመሠማራት የሚጠቅም ሆኖ አግኝተነዋል ። ያለዘመናዊ ቴክኖሎጂ ግብ አንዳችንም ከዚህ ስብሰባ ባልተገኘን ነበር ። አዎ አንዳንዶቻችንም በቴክኖሎጂ ተጨቁነናል ። ቦታዎቻችን ተወረውብናል ወይም ኤኮኖሚያችን የቴክኒክ ኃይል ባላቸው ሰዎች (አገሮች) ፈሩን ለቋል ፣ ተጣሟል ። ሁላችንም ያለአግባብ በማዋል የቴክኖሎጂ ኃይል ሥጋት አለብን ። ደስታችንም ሆነ መከራችን የአለን የዓለም አስተሳሰብ ሌሎችም ነገሮች ሁሉ በኅብረተሰቡ ባለን ቦታ የተመሠረቱ ናቸው ። የተጠበቀና በራሱ ላይ ሥልጣን ያለው ሞራል ለማግኘት እንጥራለን ። ልማዳዊ የኤቴክስ ዘዴዎች ለማኅበራዊ ሁኔታዎች ምንም ትኩረት የላቸውም ። በእምነታችን መሠረት እግዚአብሔርን የሚያየው "አዋቂ" ነኝ ባይ ሳይሆን ልበ ንጹሕ ነው ። የእግዚአብሔርን መንግሥት በመንፈስ ድሆች የሆኑ ይወርሷታል ።

እምነት ለክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር መልስ ፣ የሕይወት ሂደትና መመሪያ ነው ። ክርስቲያኖች ወደ እግዚአሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጥሮንና በተፈጥሮ ውስጥ ያላቸውን ቦታ የሚያስተውሉ ናቸው ። የክርስቲያን ጠባይ በክርስቲያናዊ ፍቅርና እግዚአብሔርን በመገንዘብ ላይ የተመሠረተ ነው ። የእምነት ማኅበር በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ መርቆ የከፈታትን አዲስ የሰው ዘመን ያስባሉ ። ያከብራሉ ። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን እምነቷን በማስታወቅ የተለያዩ እምነቶችና የሞራል ግንባታዎች በአሉበት ኅብረተሰብ ትኖራለች ። ክርስቲያኖች የፈጣሪን ፈቃድ በመፈጸም የሰው እአምሮና እጅ ሥራ ትክክለኛና ሰላማዊ ኅብረተሰብ ለመመሥረት ከማንኛውም ሰው ጋር የምድርን ፍሬ እንደ አንድ ቤተሰብ ሆኖ የሚበላበትን ዓለም ነው ። ይህም ተስፋ በኢየሱስ ክርስቶስ እርግጠኛ ሆኖ መጽናትን ፣ ትዕግሥትንና ፀዊረ-መስቀልንም የሚጠይቅ ነው ።

እውነተኛ ሳይንስ ታማኝነትን ፣ ለእውነት ትሕትናን የሚያደርግ ፣ እጉል ጥላቻን ለማስወገድ ፈቃደኝነትን ከሙከራ እርማትን የሚቀበል ነው ። እነዚህን መተላለፍ የሳይንስና የኤቴክስን ትርጉም መካድ ነው ። ሳይንስ እውነትን ለመፈለግ ነፃነትን የሚሰጡት ባህላዊ ሁኔታዎችን ይፈልጋል ። ይሁንእንጂ እነዚህ በሳይንስ ውስጥ ያሉ ነገሮች ሰብአዊነት ከአልተጨመረባቸው ፍጹም መሆን አይችሉም ። የሳይንስ ብቃት ከፍቅርና ከፍትሕ ጋር ሊገናኝ ወይም ላይገናኝ ይችላል ። የሳይንሳዊ ጥናት አቅጣጫና ተግባራዊነት ሳይንቲስቱን ከበውት በሚገኙ በባህላዊ ዋጋዎች ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ድርጅቶችን ጭምር በማጠቃለል ላይ የተመረኮዘ ነው ።

በኤቴክስና በቴክኖሎጂ መካከል የሆነ ግንኙነት አለ።አንዳንዶቹእንዳሉት ቴክኖሎጂዎች ሰው ችግሩን ሊያቃልልበት የተሰጡት የብልህነቱና የአስተዋይነቱ ውጤቶች ናቸው ። ቴክኖሎጂ ከብዙ በሽታዎች ያድናል ፣ ብዙ ምርት ያመርታል ፣ በፍጥነት ያገናኛል ። ስለዚህም ሰዎች በቴክኖሎጂ በመታጠቅ አንዳንድ ችግሮችን በማስወገድ ወደ ነፃነት ሊያመሩ ይችላሉ ። አንዳንዶችም የጉዳት መልኮቹን ይገልጣሉ ። ብዙዎችም ቴክኖሎጂ የኃይል ዓይነት በመሆኑ በኤቴክስ በኩል አስቸጋሪ ነው ይላሉ።

የኛ ቡድን ግን ሰብአዊ ማኅበራዊና የኤቴክስ ችግሮች በቴክኖሎጂ ብቻ ሊፈቱ አይችሉም ይላል ። የቴክኒካልና ሶሻል ሂደቶች ወደ ውሳኔ ከመሄዳቸው በፊት በኤቴክስ በኩል የሚያመጡትን ሁኔታ ማየቱ መልካም እንደሆነ እንገልጣለን ።

እንደ ክርስቲያንነታችን ለኤቴክስ ውሳኔ በቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ ከሁሉ በላይ በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገለጠው በእግዚአብሔር መሠረት እናደርጋለን ። ክርስቲያኖች ለሚያደርጉት ውሳኔ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት ምሳሌዎችና ሀሳቦች መሠረታውያን ናቸው። ይህን በምናረጋግጥበት ጊዜ አንዳንዴ የሚያከራክሩ ሁለት ነገሮች አሉ ።

1. ለኤቴክስ ጥያቄዎቻችን መጽሐፍ ቅዱስን እንደመልስ መጽሐፍ አንቆጥረውም ። መጽሐፍ ቅዱስና የክርስቲያን ሊቃውንት ክርስቲያኖች ዛሬ ሊያደርጉት ከሚገባቸው ውሳኔዎች ላይ እርግጠኞች ናቸው ። ለምሳሌ በጄኔቲክስ ውስጥ ስለሚካሄደው ፍሊጋ ኤቲካል ግምገማ ።

2. በአዲስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ መጽሐፍ ቅዱስ አርጅቷል ወይም ያረጀል ብለን አናስብም ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ከማያስፈልግበት ጊዜ አልደረሰንም ። የዚህ ዓይነት ጊዜም አለ ብለን አናምንም ።

ሳይንስና ኤቴክስ ብዙውን ጊዜ የሚያጠራጥሩ ነገሮችን ይሠራሉ ። የሚያጠራጥሩትም ከዕውቀት ጉድለት የተነሣ ነው ።

የክርስቲያኖች ውሳኔ የሚከተሉትን ያቀፍ ዳል ።

1. በኢየሱስ ክርስቶስ ያለጥርጥር ማመን ፤ ይህም እምነት በላቦራቶሪ ወይም በሀሳብ የሚረጋገጥ ዓይነት አይደለም ፤ ነገር ግን አንድ አማኝ ለሕይወት ራሱን አሳልፎ የሚሰጥበት እውነታ ነው ።

2. ለሰው ዘር ጥቅም የሚያስፈልጉትን ድርጊቶች ለይቶ የማወቅ ሁኔታ አጠራጣሪ ነው ። ክርስቲያኖች እንደሌሎች ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን የሚያውቁበት ጊዜ መኖሩ ባያጠራጥርም ፤ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ከመፍቀዱ ላይ ግን አጠያያቂ ነው ። ክርስቲያን የኢየሱስን ስቅለትና ትንሣኤ በማስተዋል በተመሰቃቀለው ማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ፍቅርና ፍትሕ ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ ይፈልጋል ።

ፍትሕ ተንቀሳቃሽ ሂደት ነው ፣ ለመመሥረት ግን ብዙ ጥረት ይጠይቃል ። የሰው ዘር ከተፈጥሮና ከአካባቢው ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ሊያደርግበት የሚችለው ህልውናው የተጠበቀ ህብረተሰብ ምሥረታ የረጅም ጊዜ ዕቅዱ ነው። የክርስቲያናት ስሜት በምናደርገው ሙከራ ተገልጦ ፣ በአሁኑ ጊዜ የአሉን የተፈጥሮ ሀብቶች በደንብ ቢዳረሱ በመሬት ላይ የሚገኝ ሕዝብ ሁሉ ከፈጣሪ ያገኘውን ጸጋ ይካፈል ነበር ። ማንኛውም ለዚህ ዓይነት ኅብረተሰብ መሥረታ ልባዊና ተግባራዊ ተሳትፎ ቢያደርግ ችግሮች በመፍትሔዎች ይፈታሉ ። የህልውና መጠበቅ የፍትሕ ተንጻኝ ከመሆኑም ሌላ ፣ የእግዚአብሔር ስጦታ ለኛ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ለሚመጡት ትውልዶች ጭምር መሆኑን የሚያሳስብ ነው ። ያሉን የተፈጥሮ ሀብቶች የተወሰኑ መሆናቸውን ማወቅ የማንም ሰው ፈንታ ነው ክርስቲያኖችንም እንደሚገባን ማንኛውም ሰው በኃላፊነት በነዚህ ሀብቶች የመጠቀም እኩል መብት አለው ። ስለሆነም ማንም ግለሰብ እንደራሱ ፍላጎት በመወሰን ሌላው ሕዝብ እንዲገለል መሆን የለበትም ።

ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔር መንግሥት የጽድቅና የሰላም ቦታ መሆኗን ይመሰክራል ። መንግሥቱን እንድንሻ እግዚአብሔር የአደረገልንን ግብዣ ቸል ልንለው አይገባም ። እግዚአብሔር ስለ ሥራው መከናወን ይሠራል ። ሥራውም ለሰው ልጅ ሁሉ ጉልህ በሚሆንበት መንገድ እኛ በተግባር መግለጥ አለብን ።

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ሕግ በተፈጥሮና በታሪክ ውስጥ ዛሬም በመላው ዓለም እንዳለና እንደሚሠራ ክርስቲያኖች ያምናሉ ። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል በማክበርና ትእዛዙን በመፈጸም ከሌላው የኅብረተሰብ አካል ጋር በመተባበር ለተነጋገርንበት ኅብረተሰብ ምሥረታ ግምባር ቀደም መሆን ይገባቸዋል ። እግዚአብሔርም ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ፈጣሪ ፣ ቤዛና የሰላም የፍትሕና ፣ የእኩልነት ፣ የነፃነት ምንጭ መሆኑን ለዓለም በዕለት ተግባራቸው ማስታወቅ አለባቸው ። በክርስቲያን ማኅበረሰብ የሚካሄደው ጸሎትና አምልኮ መላው የዓለምን ሕዝብ በዓለም አቀፍ ፍጹም ወንድማማችነትና እህትማማችነት የሚገኝበትን ኅብረተሰብም የሚያስታውስ በኅብረት ላይ የተመሠረተ የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ያልተለየው መሆን ይገባዋል ።

ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉና የማኅበራዊ ኑሮ መመሪያዎች ምንድር ናቸው?ብለን በጠየቅን ጊዜ ፣ ወዲያውኑ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ ሁኔታዎች መሆናቸውን እናስታውሳለን ። የአንዱ አገር ቤ ክ ከሌላው አገር በተለየ ሁኔታ ይገኛል ። ስለዚህም ለሁሉም ቤ ክ አንድ ዓይነት ጥሪ ለማስተላለፍ ያስቸግራል ። ይሁን እንጂ በተለያዩ አገሮች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔር ህልውና በየትም መሆኑን አውቀው እንደአስፈላጊነቱ ለመመሪያቸው ቅርጽ መስጠት አለባቸው በመሆኑም የሚመቻቸውንና የሚያስፈልጋቸውን እንዲያደርጉ እየጠየቅን ፣ ለአብያተ ክርስቲያናት ጥሪ እናስተላልፋለን ።

1. በጠቅላላው በዓለም ውስጥ ፤ በተለይ በብቸኞችና በተሰቃዩ ሰዎች መካከል የመገኘት ጥሪ
2. በአባሎቻቸውና በሌሎችም ሰዎች መካከል ስለእግዚአብሔር ጸጋና ፍርድ የመመስከር ጥሪ
3. የእግዚአብሔርን መገለጥ ከሰው አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በማዛመድና በምስቅልቅሉ ዓለም ስለአለው የውሳኔ አሠራር ችግሮች የማስተማር ጥሪ
4. በአዲስ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዓለም ፣ ከመማሪያና ከኃይል ክምችት መሐል ሰብአዊነት ከፍ የሚልበትን መንገድ በማስ

ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ሰሙነ ሕማማት

ከፋሲካ በፊት ያለው ሳምንት በግንኛውም ቤተ ክርስቲያን የጌታችንና የመድኃኔታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሕማማትመታሰቢያ ሳምንት ነው ፤ ግን በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተለያየ አጠራር አለው። እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት "ሰሙነ ሕማማት" ይባላል ፤ የመከራ ሳምንት ማለት ነው ። በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ (ሖሊዊክ)ቅዱስ ሳምንት ይባላል ፤ እስከ አራተኛው ምእት ዓመት ድረስ ከአርባ ጾም ጋር ሳይሆን ለብቻው ይታሰብ ነበር ። ምክንያቱም ጌታችን ፀዋትወ መከራን የተቀበለ አርባውን ጾም እንደ ፈጸመ ሳይሆን ሦስት ዓመታት ካስተማረ በኋላ ነውና ።

በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በ4ኛው ምእት ዓመት ላይ ከአርብዓ ጾም በኋላ ከፋሲካ በፊት ሰሙነ ሕማማት እንዲታሰብ ተጀመረ ። በዚህም ምክንያት ጾሙ ከ6 ወደ 7 ሳምንት ከፍ አለ ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን ግን በመጀመሪያ ጾመ ሕርቃል (ሕርቃሉስ ) በመጨረሻም ሰሙነ ሕማማት ስላለ የጾሙ ሳምንታት 8 ናቸው የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ግን ሰሙነ ኒቆዲሞስን"ሰሙነ ሕማማት ታደርጋለች በሆሣዕና ዕለትም ትንሣኤን ታከብራለች በዚህ መንገድ ጾሙ አርብዓ ቀናት ብቻ ይሆናል ።

በሰሙነ ሕማማት ሲፈጸሙ የሚታዩ አንዳንድ ድርጊቶች ከ4ኛው ምእት ዓመት ወዲህ የተጀመሩ ናቸው ለምሳሌ ፡— በ416 ዓ. ም በስቅለት ዕለት ዓርብ ሥርዐተ ቁርባን እንዳይፈጸም ተደረገ ። ይህም በዕለተ ዐርብ መድኃኔታችን ክርስቶስ፡— ራሱ መሥዋዕትኝ ሰዋዒ ምሥዋዕና መሠዊያ ተወካፊ መሥዋዕት ሆኖ መዋሉን ያመለክታል። በሰሙነ ሕማማትመጀመሪያ በሆሳዕና ዕለት የሚፈጸሙ አስደሳች መንፈሳዊያን ሥርዓቶች በ6ኛው ምእት ዓመት እንደ ተጀመሩ የቤተ/ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል፡ ለምሳሌ ሀ/አዕፁቀ-በቀለት/የዘንባባ ዝንጣፊ መባረክና ለምእመናን ማደል (ለ) የዘንባባውን ዝንጣፊ በመያዝ በቤተ ክርስቲያን ስልፍ ዑደት ማድረግ (ሐ) በቤተ ክርስቲያን በሮች እየዞሩ ወንጌል ማንበብና ከዳዊት መዝሙራት መዘመር የተጀመረ በ6ኛው ምእት ነው ዘንባባ የክብርና የድል ምልክት ከመሆኑም በላይ ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ሕጻናት ያደረጉለትን አቀባበል ያመለክታል (መ) በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር እንዳጠበ ፓትርያርኩ ወይም ሊቀ ካህናቱ የካህናትንና የምእመናንን እግር የማጠብ ሥርዓት በዚሁ በ6ኛው ምእት ዓመት ተጀምሮአል ።



ጌታችን ኢየሱስ በድል አድራጊነት ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ

## በሰሙነ ሕማማት የተፈጸሙ ታላላቅ ድርጊቶች

እሑድ (ሆሳዕና) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም ገባ ፤ ሕጻናትና ሽማግሌዎች በዝማሬ ተቀበሉት

ሰኞ፡— በቤተ መቅደስ ይሸጡና ይለውጡ የነበሩትን አባረረ ፍሬ ያልተገኘባትንም በለስ ረገመ የበለስ መረገም በአንጻሩ የኃጢአትን መረገም ያመለክታል ።

ማክሰኞ፡— ሰኞ ዕለት የተረገመችው በለስ ማክሰኞ ደርቃ ተገኘች ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ግብር አከፋፈል ስለ ትንሣኤ ሙታንና የዳዊት ልጅ የሚባል ማን ስለመሆኑ ከጸሐፍትና ፈሪሳውያን ጋር ተከራከረ ። በዚሁ ዕለት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በታላቅ ተግሣጽ ገሠጻቸው ማቴ፤ 23 በለምፃሙ በስምዖን ቤት ሳለ ማርያም እንተ ዕፍረት ሽቱ ቀባቸው ይሁዳ ጌታን ለማስያዝ በድብቅ ከአይሁድ ጋር የተነጋገረ ማክሰኞ ነበር ።

ረቡዕ፡— በዚህ ቀን የተመዘገበ ድርጊት በአራቱ ወንጌላት ሁሉ አልተገኘም ፤ ግን እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና እንደ ሌሎችም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ትውፊታዊ ትምህርት አይሁድ ጌታን ለመግደል ምክራቸውን የፈጸሙ በዕለተ ረቡዕ ነው ። ከዚህም የተነሣ ረቡዕ እንዲጾም ተደርጓል ።

ሐሙስ፡— ሐሙስ ጠዋት የፋሲካን በዓል እንዲያዘጋጁ ጌታ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ወደ ከተማ ላከ ማታ ለመጨረሻ ጊዜ የፋሲካን በዓል ከደቀመዛሙርቱ ጋር አከበረ በዚሁ ዕለት የኦሪቱን ሥርዐት ለውጦ ሐዲስ ሥርዓተ ቁርባን ሠራ በጌቴ ሴማኒ ጸለየ ይሁዳ የአይሁድን ጭፍሮች በመምራት ጌታን ያስያዘው በዕለተ ሐሙስ ነበር።

ዐርብ፡— ጌታ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ያሉትን ፀዋትወ መከራ ሁሉ ተቀበለ ተሰቀለ ሞተ ተቀበረ በዚህም ቀን ሰባት ተአምራት ተፈጽመዋል ፤ 1 .ፀሐይ ጠቆረ 2. ጨረቃ ደም ሆነ 3. ከዋክብትም ወደቁ 4. መቃብራት ተከፈቱ 5. ሙታን ተነሡ 6. አዕባን ተከፋፈሉ 7. መንጠላዕተ ቤተ መቅደስ ለሁለት ተከፈለ ፤

ቅዳሜ፡—ጌታችን በመቃብር ዋለ መቃብሩም በዘበኞች ተጠበቀ

የሰሙነ ሕማማት ሥርዐተ ጾም
እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ ቤተ ክ
ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



## የሴቶች ዐምድ

# ድንኳን ሰፊዋ ወይዘሮ

"የማይሠራ አይብላ" የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት እድሜና ጾታ ሳይለይ የተማረውም ሆነ ያልተማረው እያንዳንዱ ሰው እንደ አቅሙና ችሎታው ሰርቶ መብላት እንዳለበት የሚያመለክት ቃል ነው ። ይህም ቃል ዛሬ በኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ዋና መርሆ ሆኖ ይገኛል ።

ይሁን እንጂ ቀደም ባለው ጊዜ "መከሩ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች" ተብሎ በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተነገረው ሁሉ ይሆ ሥራ የማሃይም ነው ያኛው የገበሬ ሳይሉ በከተማም ሆነ በገጠር በተገኘው የሥራ ዓይነት ተቀጥረው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ይረዱ የነበሩት በጣም ጥቂቶች ናቸው ። አብዛኛዎቹ ግን የእነ ከሌ ወገን እንዴት ይህንን ሥራ እንሰራለን ሌላዎቹም ዘር አሰዳቢዎች እንባላለን እያሉ በመሸማቀቅ ጦም አዳሪዎች አጥንት ቆጣሪዎች ወግ አጥባቂዎች እንደነበሩ የማይታበል ሃቅ ነው

እንደዚህም ስንል በዛሬው ጽሑፋችን ስላለፈው ስርዓት ለመጻፍ ሳይሆን ይህ ዝቅተኛ ሥራ ነው ሳይሉ ሌት ተቀን ከሚሠሩት ታታሪ ሴት ከወ ሮ ዝለያቸው በዛብህ ጋር ያደረግነውን ውይይት ለመጽሔታችን ተከታታዮች ትምህርት ይሰጣል ብለን ስላመንበት ለአንባቢያን አቅርበናል ።

ትንሣኤ፡- ወ ሮ ዝለያቸው ቤተሰቦችዎን በምን ዓይነት ሥራ ያስተዳድራሉ?

ወ ሮ ዝለያቸው፡- ቤተሰቦቼን የማስተዳድረው ድንኳን በመስፋትና አንዳንዴም ጥጥ ፈትዬ በመሸጥ ነው ።

ትንሣኤ፡- ድንኳን መስፋትን ከየት ተማሩት ?

ወ ሮ ዝለያቸው፡- ድንኳን መስፋት የተማርኩት ከባለቤቴ ነው ምክንያቱም ባለቤቴ የቤተ መንግሥት ድንኳን ሰፊ ስለነበሩ እርሳቸው በትርፍ ጊዜአቸው እንዲሰፉት የሚመጣውን ድንኳን እቤት ሲቀዱ እይዝላቸዋለሁ በዛን ጊዜ እያለሁ ሲሰፉ አግዛቸዋለሁ እንዲያ ሲል ለመማር ቻልኩ አሁን እንኳንስ እኔ ትንሹ ልጇ እንኳን ሊሰፉ ሲሄዱ አብሮ እየሄደ ስላጠና ዛሬ ግማሽ ቀን ሲማር ግማሽ ቀን እኔን ያግዘኛል ። አብረንም እንሰራለን እርሱም የ19 ዓመት ልጅ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነው ።

ትንሣኤ፡- የሚሰፉት ድንኳን ለቤተ ክርስቲያን የሚያገለግል ነው ? ወይስ ለሌላ ?

ወ ሮ ዝለያቸው፡- የምሰፋቸው ድንኳኖች ለቤተ ክርስቲያን የሚያገለግልም ሆነ ለእድር እንደዚሁም በግል ለሽርሽር እንደየሰው ፍላጐት እሰፋለሁ በተለይ ግን በብዛት የሚያሠራው እድርተኛ ነው ቢሆንም ለቤተ ክርስቲያን የሚሆንም ራቅ ካሉ ቦታዎች ሳይቀር እየመጡ ያሠራሉ ለምሳሌም ከሰላሌ ፤ ከአንኮበር እና ከሌላም ቦታ መጥተው ሠርቻላቸዋለሁ ።

ትንሣኤ፡- ሕዝቡ ድንኳን መስፋት እንደሚችሉ እንዴት አውቆ ነው ዛሬ እየመጣ የሚያሰፋው ?



ወ ሮ ዝለያቸው ድንኳን ሲሰፉ

ወ ሮ ዝለያቸው፡- ሕዝቡ መቸም ድሮ ባለበቱ አቶ ተፈራ ገ ኢየሱስ በህይወት በነበሩበት ጊዜ በጣም የታወቁ የቤተ መንግሥት ድንኳን ሰፊ ስለነበሩ የሚያውቋቸው ሰዎች እንዲሰፉላቸው እቤት እምጥተው ሲሰጡአቸው ድንኳኑን ቀደውልን ወደ ሥራቸው ሲሄዱ እኛ ገጣጥመን ስፍተን እንቆያቸዋለን የሚታረም ካለው ያርሙልናል በእንዲህ ዓይነት መንገድ በባለቤቴ የሥራ ችሎታ ሕዝቡ ቤታችንን ስለለመደው ባለቤቴ ከሞቱም በኋላ ህዝቡ እንደ ልማዱ ይመጣል እኔና ልጄም በደንብ በጥሩ ሁኔታ ስለ ምንሰፋ አሁንም አሰፊው ከአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ከአንኮበር ፤ ከሰላሌ ፤ ከናዝሬት ከዱከምና ከሌላ ከሩቅ ቦታ ሁሉ እየመጣ ያሰፋል ።

ትንሣኤ፡- አንዱ ትልቅ ድንኳን ነው የሚባለው ስንት ጣቃ ይፈጃል ትንሹስ ስንት ጣቃ ይሆናል ደግሞስ ይህን ለመስፋት ስንት ጊዜ ይፈጅባችኋል ?

ወ ሮ ዝለያቸው፡- ትልቁ ድንኳን የሚባለው ከ15-18 ጣቃ ይፈጃል ይህንንም ለመስፋት ባልሳሳት ሁለት ወር ይወስዳል ከ8-12 ጣቃ መካከለኛ ነው እርሱም አንድ ወር ይወስዳል ። ከዚህ ሌላ ግን ከ3-6 ጣቃ የሚፈጅ የታቦት ድንኳን ነው ።

ትንሣኤ፡- ለመሆኑ ይህንን ሥራ የሚያካሂዱት የት ሆነው ነው ?

ወ ሮ ዝለያቸው፡- ድንኳኑን የምሰፋው እዝች ከምታዩት መኖሪያ ቤቴ ውስጥ ሆኜ ነው መችም ብነግርሽ ይገርምሻል የቤታችን ስፋት ይህችው እንደምታያት አንዲት ክፍል ቤት፤ ትንሽ ጓዳና ትንሽ ማድቤት ናት እዝች ቤት ውስጥ ስምንት ቤተሰቦች እንቀመጣለን በዛላይ የሚሰፋ ድንኳን ይመጣል እንደገና የቤት ጠቃቅን እቃም አለ ተፋፍገን እንኖራለን ። ያም ሆኖ ግን ፈጣሪዬን በጣም አመሰግናለሁ ሙሉ ጤና ሰጥቶ ከነቤተሰቤ እየሠራን እንድንበላ ፈቃዱ ስለሆነ ነው ። ልጆቼም እንደሌላው ልጆች አይደሉም ሌላ ቀርቶ ድንጋይ እንኳን ወርውረው አያውቁም ይህም ስልሽ እህትሽ ቀልድ አላቅም የሠርቶ አደር ልጆች ናቸውና ሥሩ ብዬ እንደየአቅማቸው ሥራ ሰጥቸ በሥራ እጠምዳቸዋለሁ ትምህርት ካለም ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ በደንብ ቀጥቼ ነው የማሳድጋቸው ግን ከእኔ ቅጣት ጋር የእግዚአብሔር እርዳታ ተጨምሮበት እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነን ።

ወ ሮ ዝለያቸው በተጨማሪ መግር የሚፈልግ ቢኖር እውቀተዎን ማካፈል ይፈቅዳሉ ወይ ? ብለን ለጠየቅናቸው መልስ ሲሰጡ ሰው እንኳንስ ሊማር እኛ ስንሰፋ እንኳን ሲያይ እንደ ነውር ይቆጥረዋል እንጂ እኔማ ምን ከፍቶኝ ብለዋል ። በዚህ አጋጣሚ በዚሁ ቀን እኛ ስናነጋግራቸው ሰዎች ድንኳን ለማሰፋት መጥተው ስለነበር ስለወ ሮ ዝለያቸው አስተያየት እንዲሰጡን ጠየቅናቸው አቶ ካሣ ወዳጆ ሥራቸው ግብርና የሆነ ከድኩም የመጡ በመጀመሪያ ባለቤታቸው በጣም ጥሩ ድንኳን ሰፊ ነበሩ አሁንም ወ ሮ ዝለያቸውና ልጃቸው በሰውየው እግር ስለተተኩ ሕዝቡ ከድሬ ፤ ከዳሎታ ፤ ከናዝሬትና ከዱከም እዚህ ድረስ እየመጣ ያሰፋል ስራታቸውም በጣም የታወቀ ነው ብለው አስተያየታቸውን ሰጥተውናል ።

እንግዲህ ሴቶች ወ ሮ ዝለያቸው በከፍተኛ 15 ቀበሌ 23 የሚኖሩ ሥራ ክቡር ነው የሚለውን መርህ ተከትለው የሥራን ዓይነት ሳይመርጡ ሌት ተቀን እየሠሩ ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩ ትጉህት ሴት ስለመሆናቸው ከላይ የሰጡትን ቃል ሰምተናል ስለዚህ እኛም የእኝህን እናት አርዓያ ተከትለን ለሥራ እንነሳ የሥራም ትንሽ የለውም የሥራ ቀንም ዛሬ እንጂ ነገ አይደለምና ዛሬውኑ እንሥራ ።

ብርሃን ተድላ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና አብያተ ክርስቲያናት

### የቤተክርስቲያን ታሪክ አዋቂው ጡረታ ወጡ

ጀርማንስታት ሮማንያ ፕሮፌሰር ሉድዊግ ቢንደር፦ በተባበሩት የፕሮቴስታንት ነገረ መለኮታዊ ተቅዋም ለ20 ዓመታት በቤተ ክርስቲያናዊ ታሪክ ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ በ65 ዕድሜያቸው ዕረፍት እንዲያገኙ በጡረታ ወጥተዋል ። ጠእርሳቸውም ወንበር ፕሮፌሰር ጳውሎስ ፊልፓይ ዘሄድል በርግ ለአንድ ዓመት ያህል የሚተኩ መሆናቸውን ሉተራን ወርልድ ፌዴሬሽን አስታወቀ ። (ጥር 16፡1980 እ ኤ.አ)

### 50.000 መጽሐፍ ቅዱስ ለችኮዝሎቫኪያ ተሰጠ

እስቱትጋርት ምዕራብ ጀርመን የተባበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በእስሎቫያኒክ ቋንቋ የተጻፈ 50.000 መጽሐፍ ቅዱስ በችኮዝሎቫኪያ ለሚገኘው ለሉተራን ቤተ ክርስቲያን ልኳል ። ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ 265.000 የስዊዝ ፍራንክ የሚያወጣ መሆኑን የተባበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ባለሥልጣኖች ያስታወቁ ሲሆን ፕሮፌሰር አንደርጅብራዞም ስለተላከው መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያናቸው በደስታ የተቀበለችው መሆንዋን ገልጸዋል ።

ኢኩሙኒካል ፕሬስ ሰርቪስ
ቁጥር 1/46ኛ ዓመት
ጥር 10 ቀን 1980 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ)

### የራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለሀንጋሪው ፕሮፌሰር ሽልማት ሰጠች

ቡዳፔስት ሀንጋሪ የራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ፒሜን የቅዱስ ሰርጊየስን 3ኛ ዲግሪ በቡዳፒስት ለምትገኘው ወንጌላዊት ሉተራን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ፕሮፌሰር ለሆኑት ለዶክተር ጊዩነ ናጂ ሰጥተዋል ። ሽልማቱም በአውሮፓ አብያተ ክርስቲያናት በተከናወኑት ጉባዔያት ለአምስት ዓመታት ላበረከቱት ዓለም አቀፍ አገልግሎት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ነው ይህም ሽልማት የተሰጠው በቅርቡ በክሬት ተደርጎ በነበረው የአውሮፓ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ በታሊንና በኤስቶኒያ ሜትሮ ፖሊት አሌክሲይ ነው ።

ሉተራን ወርልድ ፌዴሬሽን ቁጥር 1 80/ ጥር 8 ቀን 1980 ዓ.ም እ.ኤ.አ.

# ሰሙነ ሕማማት ...

ከገጽ ፤ የዞረ

ርስቲያን ሥርዐት ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከአርብዓ ጾም የተለየ ጾም እንዲጾም ትእዛዝ አለ ፤ ይኸውም ጾሙ እስከ ፀሐይ ጥልቀት ሲሆን የሚበላውም ደረቅ ቂጣ በጨው ብቻ እንደሆን ይኸው የቤ ክርስቲያን ሥርዐት ይናገራል ። ከዚህም ሌላ "ግብረ ሕማም" የተሰኘው ስለጌታችን ፀዋትወ መከራ የሚናገረው መጽሐፍ በየሰዓቱ ተመድቦ ይነበባል ። በዕረፍት ያሉ ምእመናንና ካህናት ከጡዋቱ እስከ ማታ በስግደትና በጸሎት ተወስነው በቤተ ክርስቲያን ይውላሉ፣ ሐሙስ ከሌሎች ቀናት የተለየ ሥርዐት ይፈጸማል። ይኸውም ቅዳሴ መቀደሱና ሕፀበተ እግር መፈጸሙ ብቻ ነው የቅዳሴው አፈጻጸም ያለ ደወልና ቃጭል በጽናጽል ነው ብዙ ዜማም አይዜምም ይህም ይሁዳ ጌታችንን በስውር ለአይሁድ እንዳስያዘው ያመለክታል። ዐርብ የስቅለት ዕለትና የቅዳም ሥዑር ዕለት የሚፈጸመው ሥርዐት ግን ራሱን ችሉ በአንድ(አርቲክል)ርእስ መጻፍ ስለሚገባው በዚሁ ጽሑፍ ላይ አላቀረብነውም ። በጠቅላላ በሰሙነ ሕማማት፦መከራ መቀበል የማይገባው ጌታችን ስለ እኛ መከራ እንደተቀበለ እናስባለን፤ የርሱም ሕማም ለእኛ መድኃኒት እንደሆነ እናምናለን እንደ ተጻፈ "ደዌያችንን ተቀበለ ፤ ሕማማችንን ተሸከመ ።--- ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፡ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን"

ሰይፈ ሥላሴ

# ሊቃውንቶቻችን

ከገጽ ፩ የዞረ

ዮጵያ የኢትዮጵያውያን ብቻ መሆንዋን ይኸንንም ትክክለኛ ቃል አለመናገርና ሕዝቡን ለትግል አለማስተባበር ፍጹም ኃጢአት መሆኑን በድፍረት ዘርዝረው አስረዱ

ጠላትም በሰጡት ቁርጠኛ መልስ ተናድዶ ከማያወላውለው ትክክለኛ ዓላማቸው በፍጹም ፍንከች የማይሉ መሆናቸውን ተገንዝቦ እንደ ነቢዩ ምናሴ ለስምንት ቀን ያህል ሌሊት በውርጭ ቀን በፀሐይ ሙቀት እያዘዋወረ ሲያሠቃያቸው ከሰነበተ በኋላ በጣም ርቆ ከተማሰ ጉድጓድ አፍ ላይ አስቆሞ ተኛዝጋች ይነሱንና ግራዝማች ተክለ ሃይማኖትን በቀኝ በግራ አድርጐ ሦስቱንም በአንድነት በመትረየስ ገደላቸው ።

በብፁዕነታቸውም ላይ ሞት የተፈረደው ኅዳር 21 ቀን 1929 ዓ.ም- ሲሆን የሞቱትም በዚህ ወር ኅዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም. ነው ።

"የጻድቃን ሞታቸው ሕይወታቸው ነው"

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል አገራቸውን እንዲሁም ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለምን ጊዜም በማይረሳ ታሪክ አስጊጠው አልፈዋል ።

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

# ዓለም አቀፍ ...

ከገጽ ፱ የዞረ

ተዋል ረገድ የአስተዋይነት ጥሪ

5. ኃይል ስለአነሳቸውና ድምፃቸው ስለአልተሰማላቸው ሰዎች በመናገር ለነርሱ የመሆን ጥሪ .
6. የለውጥና የተሐድሶ ወኪልነት ጥሪ
7. በፍትሕና በእውነት ትግሎች ሰው ነፃ እንዲወጣ የመቀስቀስ ጥሪ
8. በጋራ ምክንያት የተለያዩት አንድ ላይ የሚሄዱና የሚተባበሩ መሆናቸውን የማሳወቅ ጥሪ አለባቸው ።



# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፤ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፤ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የምን እንርዳዎ ዓምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በዚህ ዓምድ ለተለያዩ ሰዎች በቂ መልስና መፍትሔ መስጠቱን በተደጋጋሚ ተከታትዬ መረዳት ችያለሁ እኔም ሌላ ዓይነት ችግር ያለብኝ በመሆኑ ለዚሁ ችግሬ መልስ እንዲሰጡኝ በማሰብ የሚከተለውን ጥያቄ አቅርቢአለሁ ።

ስምንተኛው ሺህ እየተባለ በብዙ ቦታዎች ሲነገር ከመስማቴም በላይ በዚሁ በስምንተኛው ሽህ የክርስቶስ ምፅአት ይሆናል እየተባለ በአፍ ሲነገር ከመስማቴ በቀር በመጽሐፍ ስለ ስምንተኛው ሽህ የሚገልጽ እንዳለ ብዙ ሊቃውንትን ብጠይቅም በቂ መልስ አላገኘሁም ።

መጽሐፍ ቅዱስንም አገላብጬ ብመለከት ስለ ክርስቶስ ምፅአት ቀኑ መቼ እንደሁ አይናገርም ስምንተኛው ሽህ የሚል ቁጥር ፈጽሞ አላገኘሁም በማቴ ም. 24 ፡36 እንደሚለው "ስለዚያች ቀንና ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ የሚያውቅ የለም" ይላል ።

ታዲያ መላእክት የማያውቁትን ሰዎች እንዴት አውቀውት ነው የመምጫው ጊዜ ተቃርቦአል የሚሉት?

ስለዚህ ከዚህ በላይ ላቀረብኩት ጥያቄ መልስ ትሰጡኝ ዘንድ ዓምድህን እጠባበቃለሁ ።

ከመጽሔቱ ተከታታዮች አንዱ
ዮናስ ገብሬ

ዮናስ ገብሬ መጽሔታችንን በመከታተል ይህን የመሰለ ጠቃሚ ጥያቄ በማቅረብዎ እናመሰግናለን ። ስለ ጥያቄዎ ስምንተኛው ሽህ የሚል ቁጥር በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ም. 6 ፡5 ገጽ 520 ላይ አንድ ጊዜ ብቻ ይገኛል ። ግን ይህ ቃል በጥንቱ የግዕዝ መጽሐፍ ይገኛል ብለን የተለያዩ የጥንት መጻሕፍትን ብመለከትም ከግዕዝ ስምንተኛው ሽህ የሚል ቁጥር አላገኘሁም ።

ሆኖም ስምንተኛው ሽህ በሰዎች የቃል አነጋገር ብቻ ሳይሆን በቀመረ መጻሕፍት ይገኛል ። ብቻ እርስዎ ያነጋገሩዋቸው ሊቃውንት እነማን እንደሆኑ አላውቅም እንጂ ይህንን ቁጥር ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ስለሚያውቁት እንዴት እንዳላስረዱዎ አልገባኝም ።

ይህ ቁጥር በተደጋጋሚ የሚገኘው አቡሻኽር ከተባለው መጽሐፍ ሲሆን በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሐምሌ 30 ቀን 1962 ዓ.ም. የታተመውን ገጽ 78-79 ቢመለከቱ መረዳት ይችላሉ ቢሆንም ስለዚሁ የሚገልጸውን ባጭሩ እንደሚከተለው እንመልከት ፤

1ኛ በቀመረ ዳዊት
2ኛ በኢቤልዩ (ቀመር) ዘሙሴ
3ኛ በሱባኤ ዳንኤል
4ኛ በቀመረ ሕዝቅኤል ነው አወጣጡም እንዲህ ነው

1ኛ ቀመረ ዳዊት

ቀመረ ዳዊት አንድ ሽህ ዓመት በአንተ ፊት እንደ አንድ ቀን አለፈች ያለውን መነሻ አድርጐ ሲሆን ፤ ይህም አንድ ሽህ ዓመት 1140 ዓመት ነው ። ቅዱስ ዳዊት አንድ ዕለት ያለው ይህንን ነው ። ይህንንም ማለት 1140 ÷ 24 = 47 ከመንፈቅ ይሆናል ። አንድ ሰዓት ማለት ሲሆን መላው ለ24 ተካፍሎ 24 ሰዓት ማለት ነው ።

ይህም አንድ ሽህ አንድ መቶ አርባ ዓመት የዘመን መሥፈሪያ ነው ። 1140× 7 = 7980 ዓመት ይሆናል ።

2ኛ ኢዮቤልዩ ዘሙሴ ፤

ኢዮቤልዩ ዘሙሴ ሦስት ነው ። 3× 19 = 57 ፤ 140× 57 = 7980 ይሆናል ።

3ኛ ሱባዔ ዳንኤል

ሱባዔ ዳንኤል ሰባቱን ዓመት አንድ እያለ ነው የሚቆጥረው 19× 7 = 133 = ይሆናል 133 እስከ ስድሳ ይሄዳል ። 133× 60፡7980 ይሆናል ።

4ኛ ቀመረ ሕዝቅኤል ፤

ቀመረ ሕዝቅኤል መሰረቱ 30 ነው ። 30× 14 = 420 ይሆናል ይህም እስከ 19 ከፍ ይላል 420× 19 = 7980 ይሆናል ። የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ከላይ በጠቀስናቸው የቁጥር መንገዶች እየተመሩ ነው ስምንተኛውን ሽህ ቁጥር የሚያወጡት እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አራት ሰዎችም ሆኑ ሌሎቹ ከስምንት ሽህ በላይ ስለአልቀመሩ በስምንተኛው ሽህ ይሆናል የሚባለው ስለዚህ ነው ።

ዳሩ ግን ያቆጣጠሩ ሁኔታ ዳዊትና ቅ.ጴጥሮስ እንደተናገሩት አንድ ሽህ ዓመት እንደ አንድ ቀን ሊሆን ይችላልና አሁን ስምንተኛው ሽህ እያሉ መደናገጥ ስንፍና ነው እንግዲህ በመጠኑም ቢሆን ከዚህ በላይ የቁጥሩን አወጣጥ ለማስረዳት ሞክሬአለሁ ተግባባን ይሆን?

2ኛ ስለ ክርስቶስ ምጽአት አለመታወቅ ያቀረቡት ጥያቄ ነው ስለዚያች ቀንና ሰዓት የሰማይ መላእክት ቢሆኑ የሚያውቅ የለም ይላል ።

አዎ አሁንም ቢሆን ያለባለቤቱ በቀር ማንም ማን ስለዚያች ቀንና ሰዓት የሚያውቅ የለም ። ግን ሰዎች የክርስቶስ ምፅአት በእንዲህ ያለ ጊዜ ይሆናል መድኃኒታችን ሲናገር የሰጠውን ምልክት በመመልከት ነውና ይህንኑ ምልክትም በማቴዎስ ወንጌል ም. 24 ፡3-14 ያለውን ቢመለከቱ ማረጋ



www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፡ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ከሚያስረዳው ትምህርተ መለኮት ስለ እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር ወልድ እንዲሁም የእግዚአብሔር ወልድን ምሥጢረ ሥጋዌና ተዋሕዶውን የሚገልጥ ተከታታይ ትምህርት ባለፉት እትሞች ማቅረባችን ይታወሳል ። አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ነገረ ህላዌና ግብር ከሚገልጠው ትምህርተ ሃይማኖት የሚከተለውን አጭር ትንታኔ እናሳያለን ።

"እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ አካል ነው" ከአብ ብቻ የሠረፀ ከአብና ከወልድ ጋር ትክክል የሆነ ከነርሱም ጋር በእኩልነት ስግደትና ምስጋና የሚገባው ነው መንፈስ ቅዱስ ቅድመ ዓለም የነበረ ያለም የሚኖር ራሱን የቻለ አካል ነው ። ለመንፈስ ቅዱስ የተለየ አካል አለው ። ይህንም የሚያስረዳ ቃል ሁሉን ነገር እርሱ አንዱ መንፈስ ይሠራል ፣ ለሁሉም ለያንዳንዱ እንደወደደ ይከፍለዋል ። (1 ቆ. 12፥11) ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ አስተምሮአል ።

አብ በልብ ወልድ በቃል እንደተመሰሉ መንፈስ ቅዱስም በእስትንፋስ የሚመሰል መሆኑን ከዚህ በፊት በቀረበው አጭር ትንታኔ አይተናል ። ከሌላው ዝርው(ብትን) እስትንፋስ ለመለየትም ቅዱስ የሚለው ቅጽል ተሰጥቶታል ። መንፈስ ቅዱስን ሕፀፅ (ጉድለት) እንዳለው አድርጎ ለማሳየት ሞክሮ የነበረውን ከሐዲ (መቅዶንዮስን)ለማውገዝ ለሁለተኛ ጊዜ በቁስጥንጥንያ ተሰብስበው የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ነገረ ህላዌ ከመረመሩ በኋላ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተዋል ።

"በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን ፤ እርሱም ሕይወትን የሚሰጥ ጌታ ከአብ የሠረፀ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለንም እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ ነው ። (ጸሎተ ሃይማኖት ይመልከቱ)

መንፈስ ቅዱስ በነቢያት አድሮ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ስለማናገሩም በ2 ጴጥ 1፥20 ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ (ትእዛዝ) አልመጣም ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ጻፉት እንጂ ተብሎ ተጽፎአል ።

ለሐዋርያት የ72 ቋንቋዎችን ምሥጢር (ትርጉም) የገለጠ ፈሪዎች ለነበሩት ድፍረትን ደካሞች ለነበሩት ብርታትን የሰጠና አሁንም ይህን ሁሉ በመለገስ አማኞችን የሚያጽናና ለቤተ ክርስቲያንም ሕይወትን የሚሰጥ እርሱ ነው ነፍስ የተለየው ሥጋ በድን እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም የተለየው ክርስቲያናዊ ሕይወት እንደዚሁ በድን ነው ። በመንፈስ ቅዱስ ያልተቃኘ ሕይወት እንዳልተተኮሰ ሸክላ ይቆጠራል ።

ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል ሲናገር በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በንስሐ ይሠረይለታል መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ግን እንኳን በዚህ ዓለም በወዲያኛውም ዓለም አይሠረይለትም በማለት አስጠንቅቋል። ማቴ.12፡32

ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋውንና ምሕረቱን እንጂ መዓቱን ማነሣሣት አይገባም የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር ደስታ ሰላም፣ ትዕግሥት ቸርነት፣ በጎነት ሃይማኖት፣ ገርነት ፣ራስን (ስሜትን) መግዛት ነው ገላ. 5፥22) ለክርስቲያንም የሚያስፈልገው በረከት ይህ ሲሆን ይህ ሁሉ ስጦታ የሚገኘው ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፣

ሰፋ ያለ ሐሳብ ለማግኘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት የቀረበውን መጽሐፍ ማንበብ ይጠቅማል ።

ቆ/መክብብ አጥናው

## ምን እንርዳዎ ?

ገጥ ይችላሉ ብቻ ኃያላን ለሰዎች ሰላምና ደኅንነት ከሚያደርጉት ዝግጅት ይልቅ ለጦርነትና ለሰላም ጠንቅ የሚያደርጉት ጥረት እየከፉ በመሄዱና ይህም በየጊዜው የሚፈጸም በመሆኑ ክርስቶስ በዚህ ጊዜ ይመጣል ብሎ ዕለቱን መወሰን ባይቻልም መምጣቱ ግን ስለማያጠራጥር አንድ ሊቅ እንደተናገሩት "ምዕአት አንተ የሞትክ ዕለት ነው" ብለዋልና መልካም ነገር መሥራት የሚቻለው በቁመና እንጂ ከሞቱ በኋላ ስለማይቻል የምዕአት ጊዜ ረዘመም ቀረበም በሕይወትዎ ሳሉ መልካም ሥራ ይሥሩ ፣ ለወገንና ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ይፈጽሙ ። የጽድቅ ሁለንተናውም ይህ ነውና ።



# ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅርጻ ቅርጽ ፣ በሥነ ጽሑፍና በታሪክ የታወቀች ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፣ ከሐዋርያት ሲያያዝ የመጣውን እምነትና ባህል ጠብቃ የያዘች እንደመሆኗ መጠን በውስጥዋ የሚገኙትን እጅግ የሚያስደንቁና ውድ የሆኑ መጻሕፍትና ቅርጻ ቅርጽ በቅርስነታቸው እንደሚያኮሩና የገቢ ምንጭም እንደሚሆኑ የታወቀ ነው ። ታዲያ ብዙ ኢትዮጵያውያን ስለቅርሶቹ አጠባበቅ በቤተ ክርስቲያን በኩል ምን ያህል ጥረት እንደ ተደረገ ለማወቅ ይፈልጋሉ ፣ ስለዚህ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር የንዋየ ቅድሳትና ቅርሳቅርስ መመሪያ ኃላፊ የሆኑትን መጋቤ ካህናት ብርሃኑ መኮንን አነጋግረን ያገኘነውን መልስ ለአንባቢያን አቅርበናል ።

## መምሪያው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ምን ሠርቷል ?

መጋቤ ካህናት በመሠረቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለሀገሪቱ የታሪክ የባህል የኪነ ጥበባት የሥነ ጽሑፍ መገኛ ባለቤት እንደ መሆኗ መጠን በአጠባበቁም ረገድ ራሷን መሥዋዕት

ሳቸው ሕይወትና ከቤተሰቦቻቸው ይልቅ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የጥናት ቅርሳቅርሶችና የወግ ዕቃዎች አብልጦ በመቆርቆርና በማሰብ በየዋሻውና በየዱሩ ከዚያም በየገደሉ በመሠወር ሕይወታቸውንም ጭምር በመሠዋት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ያደረጉት ተጋድሎ በቀላሉ የሚገመት አለመሆኑን ለአንባብያን ሳንጠቁም አናልፍም በዚህም ዓይነት ኢትዮጵያ በአፍሪካ ሀገር የሥልጣኔ መዲናነት ለዓለም ሁሉ ያስመሰከረችውና ወደፊትም ስታስመሰክር የምትኖረው የታሪክ ፣ የባህል ዋጋ ያላቸው ጥንታውያን ቅርሳቅርሶቿ ባለቤት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሆኗ እርግጠኛ ሲሆን እነዚህን ጥንታውያን ቅርሳቅርዕቿ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ይህንን መመሪያ አቋቁማለች መመሪያውም ከተቋቋመ ጀምሮ በመጠኑ የሥራ እንቅስቃሴ አሳይቷል ይኸውም ጥንታውያን ንዋያተ ቅድሳትና ብራና መጻሕፍቱ በየገዳማቱና አድባራቱ ከገጠር አብያተ ክርስቲያናቱ ሳይወጡ በዚያው እንዳለ ተመዝግበው በዚያው እንዲቀመጡ ቅጽ አዘጋጅቶ በምዝገባ ላይ ይገኛል ።

ከዚህ በፊት ማለት በቀድሞው ሥርአት ተሠርቀው በልዩ ልዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች



አስደናቂ የሆነ ፱፻ ዓመት ዕድሜ ያለው የብራና ጽሑፍ

በማድረግ የፈጸመችው ውለታ ከፍተኛ መሆኑ አይካድም ለማስታወስ ያህል በሀገር ውስጥ በ9ነኛውና በ16ኛው መጀመሪያ ምዕት ዓመት በዮዲትና በግራኝ መሐመድ ወራሪነት እንዲሁም የውጭ ሀገር ወራሪዎች በየጊዜው በጠላትነት በተነሱ ቁጥር የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከራ

በመያዝ የሚገኙትን ቅርሳ ቅርሶች ሁሉ ከያሉበት በመሰብሰብ ይገኛል ለምሳሌ በ11ኛው ምዕተ ዓመት የተጻፉ የብዙ ዘመን ዕድሜ ያላቸው አራት የብራና መጻሕፍት ሁለት ስንክሳሮች ሦስት አርባዕቱ ወንጌል አራት የጳውሎስ መልእክታት በሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ በአሰሳ

ጊዜ ከማሰሰብ ቤት የተገኙትን ተረክቦ አምጥቷል ።

በተጨማሪም በ1969 ዓ.ም. ከጥር 5 ቀን እስከ የካቲት 9 ቀን በናይጀሪያ ርዕሰ ከተማ ሌጎስ ላይ ተደርጐ በነበረው የአፍሪቃና የመላው ጥቁር ሕዝቦች ኪነ ጥበባት ትርኢት በዓል ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም የበዓሉ ተሳታፊ እንድትሆን በተደረገ ጊዜ ጥንታውያን የሆኑት ታሪካዊነት የሚመሰክሩና በዓለም ፊት ተደናቂነት ያተረፉላትን ከሁለት መቶ የማያንሱ ረጅም ዕድሜ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን ዕቃዎች ማለት የብራና መጻሕፍት አልባሳትና ድባቦች መስቀሎች ጻሕል ጽዋ ልዩ ልዩ የስዕል ስዕሎችና ቅርጻ ቅርጾች የመሳሰሉትን ሁሉ ቀደምትነት ካላቸው ከየገዳማቱና ከየአድባራቱ ሰብስቦ በመምሪያው አማካይነት ንዋያተ ቅዱሳቱን ወደ ሌጎስ ልኮ አቅርቦ ስለነበረ ለጥንታዊነታቸው ለአሠራራቸው ጥበብና ኪነት ተመሳሳይ ስለታጣላቸው የዓለምን ሕዝብ አስደንቀውታል ቤተ ክርስቲያናችንንም ለዓለም ከማስተዋወቃቸውም በላይ ሀገራችንን ኢትዮጵያን ጥንታዊያን ስነጽሑፎች አኩርተዋታል በቱሪስትም በኩል ብዙ እንግዶችን የሚስቡና የገቢ ምንጭ የሚሆኑ ለመሆናቸው ተረጋግጧል የቅርሶቿም ዝነኛነትና ቀደምትነት ከዓለም ሕዝቦች ጋር ሊያስተዋውቃት ችሏል ።

እንግዲህ መመሪያው ይህንንና ይህን የመሳሰለውን ሠርቷል ። አሁንም በመሥራት ላይ ይገኛል ።

ትንሣኤ፡- መምሪያው ጥንታውያን ቅርሶች በሚገኙባቸው ቦታዎች ሙዝየም ለማቋቋም ምን ያህል ጥረት አድርጓል ?

መጋቤ ካህናት ብርሃኑ፡- መመሪያው ስለዚሁ ጉዳይ ለመነሻ ያህል በአዲስ አበባ አካባቢ ለምትገኘው እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጥንታውያን ቅርሶች በብዛት የሚገኙባት ስለሆነ እነዚህ ቅርሶች በጥሩ አያያዝ እንዲቀመጡና ለጐብኚዎች አመች ሆነው እንዲገኙ በማሰብ በአዋቂዎች ፕላን አስጠንቶ ዕርዳታ ወደሚገኝበት ክፍል በመጻጻፍ ላይ ይገኛል ።

ከዚህም ሌላ የመምሪያው ሐሳብ ብዙ ዕቅድ አውጥቷል ፣ ይኸውም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር ወደ አስራስምንት ሺህ የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ በየአንዳንዳቸው ቤተ መቅደሶች የተለያዩ ጥንታውያን ንዋያተ ቅድሳት በብዛት መኖራቸው ይታወሳል ይሁን እንጂ ቅርሳቅርሶቹ ካሁን ቀደም ማለት በአለፈው ሥርዓት ያልተመዘገቡ ስለሆነ ከመሠረቅ አልዳነም ነበር፣ምክንያቱ ሳይመዘገቡ የቆዩት የመመዝገቢያ ቅጽ ባለመዘጋጀቱ መሆኑ ግልጽ ነው ፣ አሁን ግን መምሪያው የመመዝገቢያውን ቅጽ ያዘጋጀ ስለ



www.ethiopianorthodox.org

ሆን በየክፍላተ ሀገሩ ተዘዋውሮ ከየቤተ መቅደሳቸው ሳይወጡ ንዋያተ ቅድሳቱ እንዲመዘገቡ ለማድረግ ጥረት እያደረገ ሲሆን ቅርሳ ቅርሶቹ ከተመዘገቡ በኋላ በሚገባ እንዲጠበቁም ያደርጋቸዋል ፤ በዚህ መልክ ከተመዘገቡ ዘንድ ለአጠባበቁ በክፍላተ ሀገር ርዕሰ ከተማ መለስተኛ ሙዝዩም እንዲቋቋም የተዘጋጀ ንድፈ ሐሳብ ሲሆን ከዚያም አጠቃላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናትን የሚወክል አንድ ከፍተኛ ቤተ መጻሕፍት ሕንፃ ለማሠራት ፕሮጀክት አስጠንቶ እያን ቅርሶችን ንዋያተ ቅድሳትን እንመዘግባለን ከዚህ በፊትም በጉጃም ክፍለ ሀገር በጣና ደሴት የምትገኘውን የዑራ ኪዳነ ምሕረትን ቅርሳ ቅርስና መጻሕፍት በአንድ ላይ መዝግበናል ይኸን በመሳሰለው የሥራ ግንኙነትና መቀራረብ ይኖረናል አሁንም የጋራ ፕሮግራም አዘጋጅተን ለመመዝገብ በዝግጅት ላይ እንገኛለን ።

__ትንሣኤ__ መምሪያው ወደፊት ምን ለመሥራት አቅዶአል ?

__መጋቤ ካህናት__ ከላይ በሁለተኛው ተራ ቁጥር እንደገለጽነው ንዋያተ ቅድሳትንና የብራና



ዘጠኝ መቶ ዓመት እድሜ ያለው ጥንታዊ ጽሑፍ

ቅርፁል በዚህም ከፍተኛ ሕንፃ ውስጥ የሚገኙት ጥንታውያን ቅርሶች ማለት ምትክ የሚያገኙላቸውን ልዩ ልዩ የክብር ዕቃዎችን በእንክብካቤ ለማስቀመጥ እንዲሆን ያሰበው በጠቅላላውም ንዋያተ ቅድሳቱ ከተመዘገቡ በኋላ ከዚህ የበለጠ እንደሚጠበቁና ከብልሽት ከእሳትና ከዝናም የሚድኑበትን መንገድ መምሪያው እየቀየሰ ነው ያለው ፤ በዚህም ሁሉ መጻሕፍቱ ከማንኛውም አደጋ እንደሚድኑ ተስፋ ያደርጋል

__ትንሣኤ__ ከባሕልና እስፖርት ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ምን ዓይነት ግንኙነትና አቀራረብ አላችሁ ?

__መጋቤ ካህናት__ አዎ ከፍ ያለ ግንኙነት አለን ግንኙነታችንም ስለንዋየ ቅድሳት ምዝገባ ጉዳይ በአንድነት ተባብረን የጋራ ፕሮግራም በማዘጋጀት በመምሪያው መሪነት በየገዳማቱና በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙትን ጥንታውመጻሕፍትን እንዲሁም ቀደምትነት ያላቸውን ቅርሳቅርሶች አዳዲስ የሆኑትንም ማለት ነገ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ ጥንታውያን መሆናቸው ስለማይቀር እነዚህንም ጭምር ከየቤተ መቅደሳቸው ሳይወጡ ከስርቆት ለመከላከል ያመች ዘንድ በሦስት ኮፒ መዝግበን አንዱን ለዚያው ለቤተ ክርስቲያኑ ሁለተኛውን ለሀገረ ስብከቱ ሦስተኛውን ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ ቤት አድርገን በየክፍላተ ሀገሩ እየተዘዋወርን ለመመዝገብ ፕሮግራም አዘጋጅተናል በዚሁም የየስብከተ ሀገሩ ሊቃነ ጳጳሳትና በዚሁ ውስጥ የሚገኙት ሠራተኞች ሁሉ የሥራ ትብብር እንደሚያደርጉ ስምምነት አድርገናል ይህ ዓይነቱ አሠራር የቤተ ክርስቲያናችንን ንብረት እንዳይዘርፉ ቅርሶቻችንን ለመቆጣጠር ሲሆን በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን ወደፊት ራሷን እንድትችል የሚያደርጋት ካህናቶቿም በጉብኝዎች አማካይነት የሚገኘው ገቢ በሥነ ሥርዓት ተጠብቆ እንዲሠራ ከተደረገ በዚሁ ገቢ ነው የሚተዳደሩት ማለት ነው ለዚህ ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን ንብረት መጠበቅና ማስጠበቅ የመምሪያው ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቅርሶችን ተንከባክቦ መያዝ ኃላፊነት አለበት ነው የምንለውና የወደፊት ዕቅዱ ይህን የተከተለ ሰፋ ያለ ጥናት መምሪያው ያለው መሆኑን እንገልጻለን የቤተ ክርስቲያናችን ንዋያተ ቅድሳት ከእንግዲህ ወዲህ በሌሎች ሰዎች እንደማይበዘበዙ ጽኑ ተስፋ አለን ።

__ትንሣኤ__ መምሪያው እስከ አሁን ለሠራው ያገኘው ድጋፍ ወይም እርዳታ አለ ?

__መጋቤ ካህናት__ መምሪያው ለሚሠራው ሥራ ሁሉ የሥራውን እንቅስቃሴ የተመለከቱ ብዙ ሰዎች የቃል ተስፋም ሆነ የሐሳብ ንድፍ ሙሉ በሙሉ የሞራል ድጋፍ አግኝተናል እኛም በዚህ ንድፈ ሐሳብ ለመጠቀም ከፍ ያለ ጥረት እያደረግን ነው ።

ነገር ግን እርዳታ እስከአሁን ድረስ አላገኘንም ወደፊት ግን ተስፋ አለን በምናስጠናው ፕሮጀክት መሠረት እርዳታም እንደምናገኝ እንተማመናለን ።

__ትንሣኤ__ ወደፊትስ የመምሪያውን የሥራ ይዞታ ለማሻሻል ለሚደረገው ጥረት ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ለመተባበር የሰጡት ተስፋ አለ?

__መጋቤ ካህናት__ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ለዚህ መምሪያ የሰጡት ተስፋ ድርጅቱ በሚገባ እንዲስፋፋ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት እርዳታ እንዲጠየቅና ሥራውም በበለጠ መተባበር እንዲያካሔዱ ያላቸውን ተስፋ ሲገልጹ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤም በዚህ ጉዳይ ሙሉ ትብብር እንደሚያደርግ ገልጿል ። የቤተ ክህነትም አስተዳደር ለዚሁ ሥራ እንዲስፋፋ በመጣር ላይ ይገኛል ። ይልቁንም የልማት ኮሚሽን የዓለም ዓብያተ ክርስቲያናትን የዕርዳታ ገንዘብ ለመጠየቅ ፕሮጀክት አዘጋጅቷል ይህም ተስፋ የሚጣልበት ነው ።

__ትንሣኤ__ በመምሪያው ውስጥ ስንት ሠራተኞች አሉ ?

__መጋቤ ካህናት__ በጠቅላላው ከመምሪያ ኃላፊ ጋር አራት ሠራተኞች ይገኛሉ ።

በመምሪያው ተገኝተን እንደተመለከትነው የሥራው አያያዝ ጥሩ ውጤት እንደሚኖረው ተስፋ ይደረጋል ።



## ማረሚያና ማብራሪያ

በየካቲት ወር 1972 ዓ.ም. በወጣው ትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 29 ገጽ 2 በመስመር 23 እና 24 ላይ ፤

1/ "በዓለም የታወቁ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሉአትም" የተባለው ዐረፍተ ነገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በውጭ ዓለም በደራሲነታቸው የታወቁና ድርሰታቸውም ወደ ውጭ ቋንቋ ተተርጉሞ በውጭ ዓለም ዩኒቬርስቲዎች በትምህርት መልክ የሚጠቀስላቸው ሊቃውንትና ቅዱሳን የሉአትም ለማለት አይደለም ። የዐረፍተ ነገሩ ዋና ዓላማ እንደ አባ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንደ ቅዱስ ያሬድና ቅዱስ ዜና ማርቆስ ያሉ ት በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁትን ሊቃውንት በመዘንጋት ሳይሆን ሌሎችምእንደእነርሱ በብዛት የሚቆጠሩ ሊቃውንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቁና ድርሰታቸውም ወደ ውጭ ቋንቋ ተተርጉሞ በዓለም ዩኒቬርስቲ እንዲጠቀስ አልተደረገም ይህም የሆነበት ምክንያት የመጀመሪያ መሪዎችዋ ባዕዳን ስለነበሩ ነው ለማለት ነው ። ይኸውም ብዙዎች አይደሉም በማለታችን ይታወቃል ።

2/ "የራስዋን ትምህርተ መለከት በሲኖዶስ አልወሰነችም" የሚለው ዐረፍተ ነገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ትምህርት በሠለስቱ ምእት ውሳኔ ሃይማኖት በጠቅላላ በ3 ጉባዔያት ጉባኤ ኒቅያ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ ጉባኤ ኤፌሶን አታምንም ማለት አይደለም ሦስቱን ጉባኤያት ትቀበላለች የኬልቄዶን ጉባኤንና የመሳሰሉትን አትቀበልም ። የዐረፍተ ነገሩ ዓላማ፡-በሐዋርያት ትምህርት በሠለስቱ ምእት ውሳኔ የጸናች ጥንታዊ ት ቤተ ክርስቲያን ስትሆን የምታምነውን እምነትና የምታስተምረውን ትምህርተ መለኮት ከየመድበሉ እስትጉቡዕ አድርጋ በልዩ ልዩ ቋንቋ ተርጉማ ለጐረቤት አገሮች አላከፈለችም ለማለት እንደሆነ እንዲታወቅልን ለመጽሔቱ አንባቢዎች ሁሉ እናሳስባለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# የወጣቶች ዓምድ

## ወጣት በሰበካ ጉባኤ

ከኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

ማንኛውም ሥጋዊ ድርጅት የወጣቶች ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን ስለሚያውቅ ወጣቶችን በማስተባበርና ትምህርት በመስጠት አጥፊውንም በመምከርና አንዳንድ ጊዜም በመገሠጽ የወጣቶቹን አእምሮ በእውቀት እያነፀ ብዙ ሥራ እንዲሠሩ ያደርጋል በዚህ መሠረት ወጣቶቹ እየተነቃቁ ይሄዱና ኃላፊነታቸውን ያውቃሉ ለሀገርና ለወገንም የሚጠቅም ሥራ ለመሥራት ይጣጣራሉ ።

ይህ ዓይነቱ አሠራር እስከ ዛሬ ድረስ በቤተ ክርስቲያናችን የተለመደ ባይሆንም "የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ" የሚለው ተረት ተሠርዞ ወጣቶችን ተንከባክቦ የመያዙና በቤተ ክርስቲያን ውስጥም መብት የመስጠቱ ጉዳይ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እየተለመደ የሄደ ይመስላል ። ይህ አባባል የአንዳንዶችችን የግል አስተያየት ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ሕግም ተደንግጎ ይገኛል ።

ለምሳሌ አዲስ ተሻሽሎ በወጣው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ ውስጥ እንደተጠቀሰው አንድ ሰበካ ጉባኤ ሲቋቋም የወጣቶች ጉዳይ ክፍል ሊኖረው የሚገባ መሆን በሕጉ ውስጥ መጠቀሱ የመንፈሳዊያን ወጣቶችን መደራጀትና በቤተ ክርስቲያንም የነሱ የሥራ ተካፋይ መሆን እጅግ ጠቃሚ መሆኑ የታመነበት ይመስላል፤ ምንም እንኳ በሕጉ ውስጥ ስለ ወጣቶች የተጻፈው ክፍል እስከዚህ ድረስ ሰፋ ያለ ነው ባይባልም ከቀደመው አስተሳሰብ ጋር ሲወዳደር በቀላሉ የማይገመት ርምጃ እንደሆነ መገመት ይቻላል ። ሁኔታውን በዝርዝር ለመግለጥ ያህል በዚሁ መንፈሳዊ ጉባኤ ደምብ ምዕራፍ 3 አንቀጽ 17 ላይ ስለወጣቶች ጉዳይ ክፍል ሥራና ኃላፊነት ከ1-6 ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ቃላት ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው እነዚህም፡-

1. የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበርን በሰበካው ቤተ ክርስቲያን ማቋቋም፣
2. በዚሁ ማኅበር አማካይነት የሰንበት ትምህርት እንዲሰጥ ማድረግ
3. በሰንበት ቀን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ዓበይት በዓላትና አመቺ ቀናት የዕለትና የዘወትር መመሪያ በማውጣት የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥነ ሥርዓት ፣ የሃይማኖት ትምህርት ፣ የቅዳሴ ተሰጥዎና የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት እንዲሰጥ ማድረግ ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሥርዓት እንዳይወጡም መቆጣጠር
4. የሰበካው ወጣቶች በአቋማቸውም ሆነ በጠቅላላ አኗኗራቸው ሁሉ መንፈሳውያን እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ፣
5. ለምእመናን መንፈሳዊ መልእክትን የሚሰጡ መዝሙራትን እንዲያጠኑ የሥራ መመሪያ ማዘጋጀትና መንፈሳዊ እውቀትንም እንዲያገኙ ቤተ መጻሕፍትን ማቋቋም" የሚሉ ናቸው ።

ታዲያ እነዚህ ሁሉ በየአንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመውና ወደፊትም የሚቋቋመው የሰበካ ጉባኤ ወጣቶችን እንዴት ማደራጀት እንዳለበት የሚያመለክቱ ቢሆኑም ሕጉ በቃለ ዓዋዲው ላይ ሰፍሮ ከመታየቱና ከመነበቡ በቀር በሥራ ላይ ውሎ በተግባር ተተርጉሟል ለማለት አያስደፍርም ምናልባት ፈጽመናል ብለው ለመናገር የሚሞክሩ ቢኖሩም እጅግ በጣም አነስተኞች ስለሚሆኑ ደፍሮ ለመናገር እስከዚህ ድረስ የሚያዝናና ነው ለማለት አይቻልም ። ይልቁንም በአንፃሩ በአንዳንድ ቦታዎች ስናይ የቆየነው የዚህን ተቃራኒ ነው ። ይኸውም ወጣቶቹ ከሰበካ ጉባኤም ሆነ ከካሕናት ወይም ከቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ምንም ዓይነት ድጋፍና ርዳታ ሳያገኙ በገዛ ኃይላቸው ተጣጥረው መንፈሳዊ ማኅበር በማቋቋምና መምህራን እየጋበዙ በመማር ወይም ርስበርሳቸው በመማማር ራሳቸውን አሻሽለው ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል በሚቀርቡበት ጊዜ "ዓይናችሁ ላፈር" በማለት ልዩ ልዩ ተቃውሞ የሚያደርሱና ሞራላቸው እንዲወድቅ የሚያደርጉ ወግ አጥባቂ የሆኑ አንዳንድ ግለሰቦች ከካህናትም ሆነ ከምእመናን መካከል ስለማይታጡ ነው ።

ቀና አስተያየት ያላቸውና ወጣቶችን ከቤተ ክርስቲያን ነጥለው የማይመለከቱ እውነተኞች ካሕናትና ምእመናንም በብዛት እንዳሉ አንክድም ይልቁንም አንዳንድ ዲያቆናት ወጣቶችን በቤተ ክርስቲያን በማደራጀት ረገድ ብዙ መንፈሳዊ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ለመመስከር እንወዳለን ። በዚህም መሠረት ዛሬ በየደብሩ በዓላት በሚከበሩበት ወቅት ሁሉ ወጣት መዘምራን የአባቶችን ጽናጽልና መቋሚያ ተቀብለው ታቦቱ በቆመበት ዓውደ ምሕረት ላይ በብዙ ሕዝብ መካከል ሲያስረግጡና ሲያሸበሽቡ ማየት አንድ አዲስ ምእራፍ ስለሆነ ወጣቶች ይህን መብት እንዲያገኙ ለሚተባበሩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና ካህናት ሁሉ ምስጋና ይገባል እንላለን ።

ስለወጣቶች ጉዳይ ካነሣን ዘንድ ሌላም ልናስገነዝብ የምንወደው ጉዳይ አለ ይኸውም በያንዳንዱ አጥቢያ የሰበካ ጉባኤ ውስጥ ወጣቶች ሁለት አባላት መወከል ፣ እንዳለባቸው በቃለ ዓዋዲው የተደነገገና የተወሰነ ሲሆን ይህ ምን ያህል በሥራ ላይ ውሏል? ለሚለው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የማግኘቱ ሁኔታ ነው ።

ባለፈው ዓመት ከነሐሴ 1-16 ቀን 1971 ዓ.ም. ሰበካ ጉባኤን ለማጠናከር የተመደቡት የሁለተኛው ዙር ቡድን ልኡካን በየቦታው ተዘዋውረው እንደ ተመለከቱትና እኛም በዚያው ወቅት በየቤተ ክርስቲያኑ የተቋቋመውን የሰበካ ጉባኤ ይዞታ ስንመለከት እንደተረዳነው በጥቂቶቹ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ እንጂ በአብዛኛዎቹ ፈጽሞ በሥራ ላይ ባለመዋሉ ምክንያት ወጣቶች እንኳን ፣ በሰበካ ጉባኤ አባል ሆነው እንዲሠሩ ሊፈቀድላቸው ቀርቶ ወጣቱና አዛውንቱ መልክ ለመልክ እንኳን መተዋወቅ የሚችሉ አይመስልም ፣ በሰበካ ጉባኤው ውስጥ ወጣቶች ተሳትፈዋል በሚባልበት ቦታም ቢሆን በአስተሳሰብ እምብዛም የሚጣጣሙ አይመስለንም ከዚህም የተነሣ በማናቸውም ውይይት ወቅት በመጨረሻው የድምፅ አሰጣጥ በድምፅ እንደሚለያዩ በአንዳንድ ቦታዎች በሚደርሱን አስተያየቶች ለመረዳት ችለናል ።

ያም ሆነ ይህ ልንጠቁም የምንፈልገው ወጣቶች የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ደቀመዛሙርት የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሐዋርያት ስለሆኑ አባቶች ወጣቶችን ሳይነቅፉ

ወደ ገጽ ፳ ዞሯል



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በኢኮኖሚ በኩል ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ወደ ኋላ ከሚጐትትዋት ነገሮች አንዱ በየቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ በመጠኑ የገንዘብ ምንጭ የሚገኝበትን ተግባረ እድ የመሳሰለው አለ መቋቋሙ ሁኖ እናገኘዋለን አንዳንድ የተግባረ እድ ሥራ የተቋቋሙባቸው አብያተ ክርስቲያናት ግን ጥሩ ውጤት በማሳየት ላይ እንደሚገኙ ግልጽ ነው ይሁን እንጂ "ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራም" እንደሚባለው ባለፈው መቈርቈር (ማዘን) ሳይሆን ለወደፊት ይህ የተግባረ እድ ጉዳይ በሰፊው ቢታሰብበት ረጅም ጊዜ ሳይወስድ በቅርብ ቀን ቤተ ክርስቲያናችን እንደምትሻሻልና አገልጋዮችዋንም እንደምታሻሽል አንጠራጠርም ።

አዎ ከዚህ በፊት ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት በሚል ስያሜ የሚጠራው ድርጅት በልዩ ልዩ ተግባረ እድና ትምህርት ቤቶችን በማሠራት ለኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል የሥራ ፍሬ እንዳስገኙላት በሕዳር ወር 1972 ዓ.ም. ባስተምነው መጽሔት በመጠኑ ገልጸነው እንደነበር የሚታወስ ነው አሁንም በቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ስለ ሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ልማት እንዴት እንደሆነ የደብሩን አስተዳዳሪ መምህር ተክለ ድንግልና የሰበካ ጉባኤ አባል የሆኑ አጋፋሪ ዮሐንስ መርሻን አነጋግረናቸዋል ።

ትንሣኤ፡- የዚህ የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ እንደመሆንዎ የምጠይቀዎት አዲሱ ቃለ ዓዋዲ ለሰበካ ጉባኤ የገቢ ምንጭ የሚገኝበትን ተስማሚ የሥራ መስክ በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ እንዲዘጋጁ በገጽ 22 ላይ ያመለክታል ስለዚህ በቃለ ዓዋዲው መሠረት እርስዎ ያቋቋሟቸው እንዳሉ ቢገልጹልኝ?

መልስ፡- መምህር ተክለ ድንግል በሑውነቱ እኔ ከመጣሁ እንኳን አጭር ጊዜ ነው ብዙ የተቋቋመ የለም እኔ በዚህ ደብር ከመሾሜ በፊት ግን ይህንን የምታዩት የጤፍ ክምር እንዴት እንዴት ሊያርሱትና ሊያዘምሩ እንደ ቻሉ የሰበካ ጉባኤ አባል የሆኑትን አጋፋሪ ዮሐንስ መርሻን ቢጠይቁ የተሻለ ይመስለኛል ።

ትንሣኤ፡- ይህ ሰብል በሰበካ ጉባኤ ብርታት እንደ ተገኘ መምህር ተ ድንግል ገልጸውልናል ስለዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ መሬቱን እንዴት ልታገኙ ቻላችሁ?

መልስ፡- አጋፋሪ ዮሐንስ መርሻ መሬቱን ልናገኘው የቻልነው ካህናቱና ዲያቆናቱ መዘምራኑም ሁሉ ተሰብስበው ማመልከቻ ጽፈው በትርፍ ጊዜያችን የምንሠራበት ቦታ ይሰጠን እግራችንና እጃችንን አጣምረን ብንውል ፍሬ የለውም ሲሉ ለእኛ ለሰበካ ጉባኤ አቀረቡልን እኛም የሰበካ ጉባኤአባላት በነገሩ ስለ ተደሰትንበት ማመልከቻቸውን ተቀብለን እንደ ገና እኛ ለከፍተኛ 24 ቀበሌ 17 መሬት እንዲሰጠን ብለን አመለከትን ቀበሌውም ማመልከቻችንን ተመልክቶ ከዚህ እስከዚህ ያለውን ቦታ በጥሩ ሁኔታ እንድታርሱት በማለት ቦታውን ከልሎ ሰጠን በዚህ ጊዜ መሬቱን እንደተረከብነው በመጀመሪያ ያመለከቱ ካህናትና ዲያቆናት ከ22 የማያንሱ ሁነው በዶማ መቆፈር ጀመሩ ያን በሚያዝያ 30 ቀን 1971 ዓ.ም. በዶማ ቆፍረነው የነበረውንም ሐምሌ 13 ቀን 72 ዓ.ም. ጤፍ ዘራነው ፣ ይኸውም ስንዘራው ፊት በዶማ ብንጭረውም በምንዘራበት ጊዜ የታጠቅ ሜዳ የገበሬ ማህበራት አንድ ቀን 33 ጥማድ በሬ ከነሰዎቻቸው ልኮ ከፍተኛ የጉልበት አስተዋጽኦ ስላደረጉልን ሳናመሰግናቸው አናልፍም የከፍተኛ 24 ቀበሌ 17 ደግሞ በአረም የገበሬ ማህበራት ካደረጉልን የጉልበት አስተዋጽኦ የማያንስ እርዳታ ረድተውናል ይህ አሁን የምታዩት ሰብል የዚያ ውጤት ነው ።

ትንሣኤ፡- እርስዎ ከዚህ ደብር በአስተዳዳሪነት ከተሾሙ ወዲህ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ገቢ ያስገኛል ብለው የሚያምኑት እንዳለ ቢገልጹልን?

መምህር ተክለ ድንግል በአስተዳዳሪነት ወደዚህ ከመጣሁ ከዚህ በፊት ያልነበር አጥጋቢ ፍሬ ይገኝበታል ብየ የማምነው አሁን በመሠራት ላይ ያለው ታላቅ አዳራሽ ነው ።

ይህ በቤተ ክርስቲያኑ አጥር ግቢ በመሠራት ላይ ያለው ትልቅ አዳራሽ ብዙ የሥራ እቅድ ስላለንና ዕቅዳችንንም አዳራሹ ልዩ ልዩ የተግባረ እድ ሥራ እናቋቋምበታለን ብለን ሐሳብ ስላለን ከፍተኛ ፍሬ ያስገኛል ብዬ ተስፋ የምጥልበት ይህንን ነው በተጨማሪ ከዚህ በፊት ደመና በዞረ ፣ ዝናም በዘነመ ቁጥር ምእመናኑ ብዙ ችግር ስለ ነበረባቸውና ሊያስቀድሱ መጥተው ዝናም ደብድቧቸው ይመለሱ ስለ ነበር ይኸንን ችግር በመመልከት እነሆ ከሥራ ጓደኞቼ ማለት ከሰበካ ጉባኤ ጋር በመተባበር ዛኒጋባ ሠርተን የምእመናኑ ችግር ተቃሏል ። ከዚህ ላይ ያላስታወስኩት ቢኖር አዳራሹ ለተለያዩ ተግባረ እድ ሥራዎች ብቻ ሳይሆን ለስብከተ ወንጌል

ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ/ቤ/ክርስቲያን በአፍሪካ አዳራሽ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሃገሪቱ ሂደት ውስጥ ስለሚኖራት የልማት ተሳትፎ የሚወያይ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ጉባኤ በአፍሪካ አዳራሽ ሲካሄድ ቆይቶ ተፈጸመ ።

በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርና ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተውጣጡ ልዑካን ተካፋይ የሆኑበት ይኸው ጉባኤ ለአሥር ቀናት ያደረገው ውይይት ኮሚሽኑ በሚያካሂደው የልማት ሥራ ለ3 ዓመታት ተግባራዊ በሚሆን ፕላን ላይ ተነጋግሮ ለታቀደው የልማት ክንውን የሚያስፈልገውን ገንዘብ በርዳታ ለማግኘት ስለሚቻልበት ሁኔታ አትኩሮት ሰጥቶት ቆይቷል ።

በውይይቱም ወቅት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን ዘንድ 59 እቅዶች አቅርቦ ጉባኤው እነዚህን እቅዶች አጥንቶ የሚያቀርብ ኮሚቴ መርጦ ከአሁን በፊት በእርዳታ ሰጭዎች የተሠራውን ሥራ ለመጎብኘት በየምድባቸው ሄደዋል ። የጉብኝት ሥፍራዎቹም 1ኛ አዲስ አበባና አካባቢዋ 2ኛ ሐረር 3ኛ ባሕር ዳርና ጐንደር ነበሩ ። ይህንን ም የጉብኝት ጊዜአቸውን ጨርሰው እንደተመለሱ ስብሰባው ቀጥሎ ሁሉም በየምድባቸው ያዩትን ሪፖርት በማቅረብ ብዙ ከተወያዩበት በኋላ መሻሻል ያለበት እንዲሻሻል ጥሩ የሆነውንም እንዲቀጥል በማለት ወስኗል ። በዚህም ጊዜ ቀደም ብሎ እቅዱን አጥንተው እንዲያቀርቡ የተመረጡት ሰዎች 59ኙን እቅዶች በ10 በማጠቃለል ስላቀረቡ ጉባኤው አንድ በአንድ ተወያይቶባቸው የመጨረሻ ውሳኔ አስተላልፏል ።

የጉባኤው ዋና ዓላማ የኢትዮጵያ ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም አቅጣጫ ሕይወት እንዲኖራት በአገልግሎት ፣ በፍትህና በተልዕኮ መካከል ምንም ዓይነት መበላለጥ ሳይኖር ለማሠራት የሚል መንፈስ የተመረከዘ ሲሆን የቀረቡት አሥሩ አጠቃላይ እቅዶች 1ኛ/የካህናት ማሰልጠኛ ፕሮግራም 2ኛ/የሰበካ ጉባኤ ፕሮግራም3ኛ የወጣቶች መንፈሳዊያን ማህበራትና ሰሚናሮች 4ኛ/ገዳማት 5ኛ/የአካባቢ ልማት እቅድ 6ኛ የልማትና የተራድኦ ኮሚሽን ዓመታዊ ባጀት ፣ 7ኛ/የመንፈሳዊ ኮሌጅ መከፈት 8ኛ/ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ 9ኛ የመሪዎች ማሠልጠን እና የሰራተኞች እድገት 10ኛ/ ልዩ ልዩ እቅዶች ፕሮጀክት ለምሳሌ እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እና ሙዝየም ከነዚህ ውስጥ ቅድሚያ የተሰጣቸው ፡—

1ኛ ጠቅላላ ጉባኤው ለካህናት ማሠልጠኛ ፕሮግራም የሚውል ገንዘብ ለማዋጣት ቃል ገብቷል ይኸውም ጠቅላላ መዋጮው 1.121.700 የኢትዮጵያ ብር/ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ በዓመት ከብር 421 . 700 (አራት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ብር) ያልበለጠ ለፕሮግራሙ ማካሄጃ እንዲወጣ ቀሪው ለሚቀጥሉት ሁለት አመታት 700.000 (ሰባት መቶ ሺህ ብር) ተቀማጭ እንዲሆን ።

2ኛ/ ለሰበካ ጉባኤ 725 . 000 ሰባት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ብር

3ኛ/ ለመላው የኢትዮጵያ መንፈሳዊያን ወጣት ማህበራት እስከ 50.000.- (ሃምሳ ሺህ ብር ሆኖ በመካሄድ ላይ ላለው የወጣት መሪዎች ማሠልጠኛ ፕሮግራም ለዋናው ጉባኤ ሪፖርት አቅርቦ ጉባኤው ከተረዳ በኋላ እስከ 150.000 -አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) እንዲያገኝ አቅዷል። 4/ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በልማትና ተራድኦ ኮሚሽን ውስጥ ለሚገኙት ሠራተኞች በጥሮታ ደንብ በአቀጣጠር ሁኔታና የመሳሰለውንም በ3ወር ውስጥ ለማሟላት ሙሉ ሃላፊነት የወሰደ እንደሆን በሚከተሉት ስምምነት ላይ ተደርሷል ።

ሀ ከ1980-1982 እንደ ኤሮፓ አቆጣጠር ጉባኤው ለአስተዳደሩ የሚደረገው የባጀት መዋጮ ከ900.000.-የማይበልጥ ይሆናል

ለ ጉባኤው ለልማትና ተራድኦ ኮሚሽን አስተዳደር ለ1980 የሚያዋጣው ባጀት እስከ 275.000.- ይሆናል ።

ሐ በእርዳታ ሰጭው ለልማትና ተራድኦ ኮምሽን አስተዳደር ለ1981 የሚደረገው የባጀት መዋጮ የሚተመነውና የሚወሰነው በመጀመሪያው የዋናው ዕርዳታ ሰጭ ጉባኤ ስብሰባ ላይ ነው ።

መ የ1982 ባጀት የሚወሰነው በዋናው ጉባኤ ስብሰባ በ1982 ነው ።

5ኛ ስለ ገዳማትና የአካባቢ ልማት የመሳሰሉት ትናንሽ እቅዶች የልማትና ተራድኦ ኮሚሽን አስፈላጊ መረጃዎችን ካቀረበ እያንዳንዱ በ20.000፦/በሃያ ሺህ ብር/የሚንቀሳቀሱ እስከ $200.000፦/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ወጭ በማድረግ ለማቋቋም ሐሳብ ቀርቧል ።

6ኛ/ ጉባኤው ገንዘብ የተተመነላቸው ሥራዎች ፍጻሜ እንዲያገኙ በተቻለ መጠን ወደ አጽዳቂው አካል አቅርቦ ለማስፈጸም እንደሚሞክር ቃል ሲገባ ሌሎች ረዘም ያለና ጠለቅ ያለ ጥናት የሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች ግን ጥናቱ እንዳለቀ አስፈላጊው እርዳታ የሚደረግ መሆኑን አስታውቀዋል። በዚህም ጊዜ ስለ መንፈሳዊ ኮሌጅ እንደገና መከፈት ተነስቶ ጉባኤው ተወያይቶበት ከአራት ወር በኋላ በጀኔቭ በሚደረገው ስብሰባ ላይ እንደገና እንደሚቀርብ ተነግሯል ።

በመጨረሻም ገንዘብ ያልተተመነላቸው እቅዶች ከአራት ወራት በኋላ እንደዚሁ ጀኔቭ በሚሰበሰበው ጉባኤ ላይ ኮሚሽኑ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭነት ያለውና በቂ እቅድ እንዲያቀርብ ወስና በውሳኔው ረቂቅ ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ.ቤተ ክርስቲያን ስም አቡነ መቃርዮስ የጉጃም ሊቀጳጳስ ሲፈርሙ በዓለም አብያተ ክርስትያናት ማህበር ስም ዶክተር አርን ቶለር ፈርመው የጉባኤው ፍጻሜ ሆኗል ።

---

## ወጣት ...

ከገጽ ፲፰ የዞረ

ወጣቶችም አባቶችን ሳይንቁ የቤተ ክርስቲያንን ሕልውና ጠብቀው ለሙጭው ትውልድ ለማስረከብ ይተባበሩ ዘንድ ለማሳሰብ እንወዳለን ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የሰበካ ጉባኤዎች ሁሉ በቃለ ዓዋዲው ላይ በተደነገገው ሕግ መሠረት የወጣቶችን ሕልውና ጠብቀው በሚገባ እንዲደራጁ ሲያደርጉ ነው ። በዚህም ጉዳይ የወጣቶች አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ በርትቶ በመሥራትና ሁኔታውን በመመርመር በየቦታው ያለው ችግር ሁሉ መፍትሔ እንዲያገኝ መጣጣርና ማስተባበር አለበት እንላለን ።

---

# የጤና ዓምድ

ጤንነታችንን እንዴት መጠበቅ እንደምንችል መጽሐፍ ቅዱሳችን ብዙ ምክር እንደሚሰጠን ታውቃላችሁ ?

ከሚሰጠንም ብዙ ምክሮች ጤንነታችን በምግብ በኩል እንዲሁም የጤንነታችንን ንጽሕና በመጠበቅ በኩል ከተጋቦት በሽታ እንዴት ለመዳን እንደምንችል በብዙ መንገዶች ከገለጸ በኋላ የዚህ ሁሉ ውጤት ደግሞ መደሰት እንደሚሆን ይነገረናል እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ካሟላን ወይም ከጠበቅን በመጨረሻ ውጤታችን የሚሆነው መደሰት ነው ብለናልና በዚሁ ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች እንመለከታለን። በመጀመሪያም ጤንነትን መጠበቅ ማለት በሽታ ከያዘ በኋላ ማስታመም ወይም ልዩ ልዩ መድሃኒቶችን መውሰድ ብቻ ሳይሆን ቀድሞ በበሽታ ላለመያዝ መጠንቀቅ መሆኑን እንወቅ ይኸንንም መጽሐፍ ቅዱሳችን ይነገረናል ውስጣዊ ሰውነታችን በበሽታ ያልተያዘ ከሆነ ውስጣዊ አካላችን በበሽታ መያዙ ከተሰማን ውስጣዊ ሰውነታችን ጤነኛ መሆኑ ያሰጋል ።

ስለዚህም መደሰት የሙሉ ጤንነት ውጤት ለመሆኑ ደስ ያላት ልብ መልካም መድሃኒት ናት ምሳሌ 17፡22 በበሽታ ያልተበከለ ማለት ነው ምስጋና ፣ ደግነት ፣ መደሰት ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር መታመን እነዚህ የጤና ታላቅ ጠባቂዎች ናቸው "የእግዚአብሔር ደስታ ሀይላችሁ ነውና አትዘኑ" ንህምያ 8፡10 በዚህ ክፍል መደሰት ሙሉ ጤንነትን ማግኘት መሆኑን ሲገልጽ ማዘን ደግሞ የጤንነት ሁከት እንዳለበት ያስረዳናል እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በደንቦቻቸው ረገድ ለሞራልም ሆነ ለሥጋዊው ጤንነት ዋና የሆነውን ምክር በንጽሕና አጠባበቅም ሆነ በምግብ በኩል ለይቶ ሰጥቶአቸዋል ያ ዛሬም ለእኛ ይጠቅማል እራስን በንጽሕና መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በጥብቅ አኳኋን ተናግሯል በእግዚአብሔር ቃል የታወጀውን ሕግ ለማድመጥ በሲና ተራራ ከመሰብሰባቸው በፊት ሕዝቡ ሰውነታቸውን መታጠብና ልብሳቸውን ማጠብ አስፈለጋቸው ይህም ምክር እስከ ሞት መቀጫ እንኳ የፀና ሆነ በእግዚአብሔር ፊት ንጽሕናን ያለመጠበቅ (እርኩስነት) አይፈቀድም ነበርና ከሚተላለፍ ወይም ከተጋቦት በሽታ ጋር ንክኪ የሚያደርጉ ሁሉ ከሰፈር ለብቻ ተለይተው ሰውየውና ልብሱ ንፁህ ሳይሆኑ ወደዚያ እንዳይመለሱም ይደረግ ነበር ዘሌዋ. 15.4-12 እንመልከት ።

እንዲሁም እስራኤላውያን በምድረ በዳ በሰነበቱበት ጊዜ በቅርባቸው ባሉት ቤቶች ከሚኖሩት ኑዋሪዎች ይልቅ እርኩስና ጉጂነቱ ባነሰበት ሥፍራ ዘወትር ግልጽ በሆነው ነፋሻ ዐየር ውስጥ ነበሩ ። ሆኖም በድንኳኖቻቸው ውስጥና በስተውጭም በንጽሕና ስለመሆን የጠበቀ ጥንቃቄ ያስፈልጋቸው ስለነበር በሰፈሩ ወይም በዙሪያው ቆሻሻ ነገር እንዲኖር አይፈቀድም ነበር ይህን ታሪክ ስንመለከት ንጽሕናን ለመጠበቅ መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ብንል ስህተት አይሆንም ።

ምግብ፡-እግዚአብሔር የምንበላውንም ነገር ለይቶ ሰጥቶናል ። እነዚህም ንፁሕና እርኩስ ሲል የተናገረው ቃሉን ከዘሌዋውያን ምዕራፍ 20፡24-25 እንመልከት ። በዙሪያቸው ያሉት አረማውያን እንደፈቀዱ ይበሉት የነበረው ልዩ ልዩ ዓይነት ምግብ ለእስራኤላውያን እንዳይበሉ ክልክል ነበር ። ይህም በነገሩ ልዩነት ለማድረግ አልነበረም የተከለከሉት ነገሮች ለጤና የማይስማሙ ስለሆኑ እንጂ እርኩስ መሆናቸው የተነገረው ጉጂዎችን ምግቦች መብላት የሚያረክሱ እንደሆኑ እግዚአብሔር አስተማረን አካልን የሚያረክስ ነፍስንም ወደማጥፋት ያዘነብላል የሚበላውንም ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ለመሆን የማይገባው ያደርገዋል ።

ተስፋ በተሰጣቸው ምድረ በዳ በመጀመሪያ የተሰጣቸው ደንብ የቀና ልምድ (ዐመል) ለመመስረቻ የሚስማማ በመሆኑ ቀጠሉበት ሕዝቡ በከተማዎቹ እየተጣበቡ መሰብሰቢያ አልነበራቸውም ። ግን እያንዳንዱ ቤተሰብ ጤና የሚሰጥ ለሕይወት የሚስማማ የተፈጥሮን በረከቶች ሁሉ የሚሳተፈው እራሱ የሚቀመጥበት ምድር ነበረው ።

በዚህ ሁሉና በመሳሰሉት እስራኤላውያን በዕለት ሕይወት ጉዳያቸው ሁሉ በንጽህናና በምግብ በኩል ጤንነታቸው እንዴት ሊጠበቅላቸው እንደሚችልና በዚያም ውስጥ ብዙ መደሰትንና በረከትን እንዳገኙበት በተነገራቸው የማያወላውል ቃል ተምረዋል ከንፁሐንና ርኩሳን መሀከል የመለየትን ጉዳይ ይጠብቁ የነበረው በሃይማኖታዊ አገልግሎት (ልምድ)ብቻ ሳይሆን ዕለት ዕለት በሚያደርጉት የኑሮ ጉዳያቸው ሁሉም ነው ይኀንንም ትዕዛዝ ወይም ጥንቃቄ በመቀበላቸው በጤንነታቸው በኩል ጉጂ የሆነ ነገር አልደረሰባቸውም ነበር ከዚህም ሕግ ፈቀቅ ባሉ ጊዜና ያሰኛቸውን ለማድረግ በወደዱ ጊዜ በሥጋቸው እሳት ሆኖባቸዋል ። እንግዲህ መደሰት ጤንነትን በማግኘት እንጂ ጤንነት የሌለበት ደስታ ከሚያስፈልግም በላይ እንኳ ቢገኝ ሊኖር አይችልም መደሰት የመንፈስንና የሥጋንም ጤንነት በጤንነትም ሁሉን ማግኘት ማድረግ ይቻላል

ስለዚህ የደስታችን መሠረት ጤንነት እንዲሆን አብዝተን እንጠንቀቅ ።

ወ ት ንብረት አበበ

---

## ልማት ....

ከገጽ ፲፱ የዞረ

ም የሚያገለግል ነው ።

እኔና የሰበካ ጉባኤ በዚህ ሳንወሰን ለደብሩ ጽሬት ቤት የሚሆን ለእቃ ቤት ጭምርም በመሥራት ላይ ነን ።

ትንሣኤ፡- ለወደፊት ያላችሁ ዕቅድ እንዴት እንደ ሆነ ቢያብራሩልኝ?

አጋፋሪ ዮሐንስ መርሻ ለወደፊት ያለን ዕቅድ የመጀመሪያው ትእዛዝ ወዝህን አንጠፍጥፈህ እንጀራህን ብላ ዘፍጥ 3፡17 ተብሎ የታዘዘውን አምላካዊ ትእዛዝ በመከተል አያሌ የሥራ ዕቅዶች አሉን ።

እነዚህም ማለት ያሰብናቸው ዕቅዶች 1ኛ የከብትና የዶሮ ርባታ 2ኛ/ ይህንን መሬት አሁን ካለበት አስፋፍተን የተሻለ ፍሬ የምናገኝበትን ዘዴ በመዘጋጀት ላይ ነን ።

ትንሣኤ፡- በዶማ እየቆፈራችሁ ሰፊውን መሬት ማልማታችሁ አምላካዊውን ትእዛዝ ከመፈጸማችሁም ሌላ የሚያስመሰግናችሁ ነው ይሁን እንጂ ይህን የተገኘውን ምርት ከምን ታውሉታላችሁ?

አጋፋሪ ዮሐንስ መርሻ ይህ ያመረትነው ምርት 1ኛ/ በድርቅ ለተጐዱ የተፈጥሮ ጓደኞቻችን በመጠኑ እንረዳበታለን 2ኛ/ ለልማቱ ማጠናከሪያ እናደርገዋለን 3ኛ/ ደግሞ ከዚህ የተረፈው እንደ ሥራ እንደ ሥራችን እንካፈለዋለን ስለ ወደፊት ልማት ግን የልማት ኮሚሽን አባላት ከዚህ ቦታ ድረስ መጥተው ቦታውንና ልማቱን ተመልክ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ትንሣኤ ሙታንን እናምናለን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከ መነሣቱ በፊት ሰዎች ከሞቱ እንደገና ስለመነሣታቸው አንዳንድ ሰዎች ይጠ ራጠሩ ነበር ነገር ግን በየጊዜው ከተነ ሱት ነቢያት መካከል ሆሴዕ "ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል በሦስተኛውም ቀን ያስነሳናል በፊቱም በሕይወት እንናራ



ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሣ እናምናለን

ለን'' ብሏል ሆሴዕ ምዕራ 6 ቁጥር 2 ኢሳ ይያስም ሙታን እንደሚነሡና ሁለተኛ ሕይወት እንደሚኖራቸው ተናግሮአል ኢሳ. 26፥19 ይህም አባባል ትንሣኤ ሙ

ታን እንዳለ ከመግለጹም ሌላ የሙታን በኩር የሆነው ክርስቶስ ጊዜው ሲደርስ ተነስቶ ሙታንንም እንደሚያስነሳ ይ ጠራጠሩ የነበሩትን አሳምኗል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በየጊዜው የተነ ሱት እንደ ዲሞክራቶስ የመሳሰሉት "ት ንሣኤ ሙታን የለም ከማለታቸውም ሌላ ምንም ነገር የለም ፣ ዛሬ እንብላ ፣ እንጠጣ ፣ እንደሰት ነገ እንሞታለን'' እያሉ በማስተማራቸው ብዙ ተከታዮች ሊያፈሩ ችለዋል ስለዚህ ትንሣኤ ሙታ

ን አለ የሚለው ችግር መፍትሔ ሳያገ ኝለት ለብዙ ጊዜ ቆየ እንዳንዶቹም ደግሞ እራሳቸውን አምላክ አድርገው ተነስተው ነበር ብዙ ተከታይም አገኙ እየተዘዋወሩ ሰበኩ ፣ አስተማሩ በመጨ ረሻም ሞቱ፣ከሞቱም በኋላ አልተነሱም ባለመነሳታቸውም ይነሳሉ ብሎ ያመነ ባቸው ሕዝብ ሁሉ ተስፋ ቆርጦ ተበተ ነ በዚህ አኳኋን የሙታን መነሳት በተ ከታዮቻቸው ዘንድ ትርጉም አጥቶ ቀረ

በተጨማሪም የሮም መንግሥት ደጋ ፊ የነበሩትና ትንሣኤ ሙታን የማያም ኑ ሰዱቃውያንም ቢሆኑ ትንሣኤ ሙታ ን የለም እያሉ በማስተማራቸው ብዙ ተከታዮች እንዳፈሩ ይነገርላቸዋል። ከፈሪሳውያንም ጋር በዚህ ትምህርት አይስማሙም ነበር ይባላል የዘመኑ ፍ ፃሜ ሲደርስ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም እየተዘዋ ወረ በሚያስተምርበት ጊዜ "ወደ ኢየ ሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከ ካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ን ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛው ም ቀን እንደሚነሳ ለደቀመዛሙርቱ ገ ለጸላቸው ።

እንዳለውም ተሰቅሎ ሙቶ በሦስተ ኛው ቀን በመነሳቱ በኩረ ትንሣኤ ሙ ታን ሆነ የሙታንም መነሳት መኖሩ ተ ረጋገጠ ስለዚህም ወንጌላዊው ማቴዎስ "መቃብሮች ተከፈቱ ተኝተው ከነበሩ ትም ከቅዱሳን ብዙ ሰዎች ተነሱ ። ከት ንሣኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተ ው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎ ች ታዩ'' ሲል በምዕራፍ 27 ከቁጥር 52-53 ተናግሯል ። በዚህ አኳኋን ክርስቶስ በተነሳበት ዕለት ብዙ የሞቱ ሰዎች ተነ ስተው ለብዙ ሰዎች እንደታዩና ትንሣ ኤውንም እንደመሠከሩ በመረጋገጡ ለ ብዙ ዘመን አስቸጋሪ ሆኖ የቆየው ትን ሣኤ ሙታን በተግባር ሊገለጽ ችሏል ።

በተጨማሪም ክርስቶስ ከሞት መነሳ ቱንና በትንሣኤውም ለሞቱት ሰዎች ሁሉ በኩረ ትንሣኤ መሆኑን ለማረጋገ ጥ ከትንሣኤው በኋላ አሥራ አንድ ጊዜ ለተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት በተ ለያዩ ቦታዎች ተገልጦ ታይቷል ፣ ይል

ቁንም ትንሣኤውን ለተጠራጠረው ለ ቶማስ የተወጋ ጐኑንና የተቸነከሩ እጆ ቹን በማሳየት ትንሣኤውን አሳምኖታ ል ።

በዚሁ ሁኔታ የክርስቶስ ከሞት መነ ሳትና ለሞቱት ሁሉ የትንሣኤያቸው በ ኩር መሆኑ ሊታመንበት ችሏል ሐዋር ያው ቅዱስ ጳውሎስም ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳና ትንሣኤ ሙታንም እንዳለ ሲያስተምር "ወንድሞቼ ሆይ ዕለት ዕለ ት እሞታለሁ እንደ ሰው በኤፌሶን ከአ ውሬ ጋር ከታገልሁ ሙታንስ የማይነ ሱ ከሆነ ምን ይጠቅመናል? ነገር ግን ሰዎች ከሙታን እንዴት ይነሳሉ? በም ንስዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖ ር ይሆናል አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራ ው ካልሞተ ሕያው አይሆንም የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው በመበስበ ስ ይዘራል ባለመበስበስ ይነሣል፣ በው ርደት ይዘራል በክብር ይነሣል ፣ በድካ ም ይዘራል በኃይል ይነሣል'' ብሏል አ ንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 31 -41 ።

ሐዋርያው እንዳለው ሙታን የማይ ነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሳም ማለት ነውን? ክርስቶስም ካልተነሳ እምነታች ን ሁሉ ከንቱ ነው ማለት ነው ስለዚህ በእውነት ክርስቶስ ተነስቷል ሙታን ም በአዲስ አካል በአዲስ መንፈስ ይነ ሳሉ ።

እንግዲህ "ኢየሱስ እንደሞተና እን ደተነሳ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያ ንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና'' ይላል 1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 4 ቁጥር 14 ከዚህም የተነሳ ስ ንሞት ስጋችን እንጂ ነፍሳችን አታንቀ ላፋም ስለዚህም ለቅዱሳን ሁሉ ኢየሱ ስ "ዛሬውኑ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናላ ችሁ" የሚለውን ተስፋ ሰጥቷቸዋል በኢየሱስ ያንቀላፉ ነፍሳቸውን በእግዚ አብሔር ዙፋን ፊት በቤተ መቅደስም ቀንና ሌሊት ሃሌ ሉያ እያሉ እየዘመሩ በደሙ ከኃጢአታቸው ያነፃቸውን ክር ስቶስን ያመሰግኑታል ።

ይህም የተባለው እንቅልፉ ምን ዓይ ነት እንቅልፍ ነው? ማንቀላፋት ማለት ፀጥታና ደስታ ያለበት መልካም ዕረፍ ት ነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የ ሚሞቱትና የሚነሱት ሁሉ እንዴት የ ታደሉ ናቸው? ይህም ማለት ከድካም ሥራቸው ያርፋሉ ፣ መልካም ሥራቸው ይከተላቸዋል ፀጥታ የሰፈነበት እረፍታ ቸው እግዚአብሔር ዋጋቸውን ለመስ ጠት ከእንቅልፋቸው እስኪቀሰቅሳቸ ው ድረስ መልካም ዕረፍት ይሆንላቸ ዋል ።

ይህም ማለት በሰማይ መላእክት ተ ጠብቀው የክብር ወራሾች የሆኑት ምዕ መናን ናቸው ትንሣኤያቸው እስኪደር ስ ድረስ አሸልበው ይጠባበቃሉ ማለት ነው ሲነሱ ግን ምን ዓይነት መንቃት ይነቁ ይሆን ሰዎች ሲሞቱ ሥጋቸው በ ሕማም ወይም በእርጅና ይደክማል በ ድካምና በሕማም ተጐሳቅሎ የነበረው ሰውነታቸው ዳግመኛ ሲነሱ በአዲስ አ ካል ፣ በአዲስ መንፈስ ይለወጣል የትን ሣኤ ሙታን አኳኋን የሚፈፀመው በዚ ሁ መንገድ ነው ።

ይህንን ያልተገነዘቡ አንዳንድ ሰዎ ች ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ ሰዎች ዛሬ ለምን ይሞታሉ? ከሞቱስ ለምን አይነ ሱም? የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ ስለዚህ አ ንሰል የተባለው ሊቅ "ክርስቶስ ስለ ኃ ጢአት ሞቷል እንላለን ኃጢአት ዛሬም አለ ክርስቶስ ሞትን ስላቸነፈ ሞት የለ ም እንላለን ትሞታለህ ባለው ቃል መ ሠረት ዛሬም ሰዎች ሲሞቱ እናያለን ካለ በኋላ ለዚህ አስተያየት መልስ ሲሰ ጥ የቀድሞ ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው በ መንፈስ ይሞቱ ነበር ዛሬ ግን በሥራች ን ከክርስቶስ ፊት ስለምንቀርብ መንፈ ሳዊ ሞት አንሞትም እንጂ ስጋዊ ሞት ዛሬም ቢሆን እንሞታለን'' ብሏል ።

እንዳለውም በኃጢአታችን ሙተን የነበርን ሁሉ በክርስቶስ ትንሣኤ ተነስ ተናል ስለሆነም 318 ሊቃውንት ትንሣ ኤ ሙታንን እናምናለን የሚመጣውን ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን ሲሉ በፀሎ ተ ሃይማኖት ተናግረዋል እንዳሉትም በኋለኛው የዘመን ፍፃሜ ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ በጌትነትና በምስጋና ተ መልሶ ይመጣል በዚያም ጊዜ የሞቱት ሰዎች ሁሉ ይነሣሉ ። ከተነሱም በኋላ መልካም የሠሩ ወደ ለዘለዓለም ሕይወ ት ይሄዳሉ ክፉም የሠሩ ወደ ዘለዓለም ሞት ይሄዳሉ ስለዚህ የትንሣኤያችን በ ኩር የሆነው ክርስቶስ ተነስቷልና ትን ሣኤ ሙታንን እናምናለን ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ልማት ....

ከገጽ ፳፩ የዞረ

ተው ለወደፊት እንረዳችኋለን ሲሉ ቃ ል ስለገቡልን የልማት ኮሚሽን እርዳ ታን እየተጠባበቅን ነን ሲሉ አብራርተ ውልናል ።

የቀራንዮ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስ ቲያን አገልጋዮች ሠርቶ የመጠቀም ል ምድ ስለነበራቸው በአካባቢያቸው ያለ ው መሬት የሚያርሰውና መንጥሮና ቆ ፍሮ የሚያለማው አጥቶ ጦም አደር ሁ ኖ አይተው ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያ ሳ ይኖራቸው እሱ ቀርቶ በሮች እንኳን ሳ ይጠምዱ እጃቸው እስኪላጥ ድረስ ቦታ



አባ ተክለ ድንግል
የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም አስተዳዳሪ

ውን በዶማ ቆፍረው ምን ያህል ምርት እንዳገኙ ተመልክተናል ።

እንግዲህ የችግር የእርዛት ምንጫ ቸውና መገኛቸው ምንድን ነው ብለን ራሳችንን በራሳችን ብንጠይቅ እጅንና እግርን አጣምሮ ቁጭ ብሎ መዋል ነ ው ከማለት በስተቀር ሌላ መልስ የምና ገኝ አይመስለኝም በዚህ አንጻር ደግሞ እነዚህ ሊወገዱ የሚቻላቸው ልማት በ የቤተ ክርስቲያኑ ሲስፋፋ መሆኑን እና ምናለን ስለዚህ ሁሉም ወደ ልማት መ ሠማራት ይኖርበታል እንላለን ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ





www.ethiopianorthodox.org

## የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ

### የማርቆስ ወንጌል ። ምዕራፍ ፲፮

**ኢየሱስ ለማርያም ተገለጠ**

፱ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ማልዶ በተነሣ ጊዜ ፣
አስቀድሞ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለመግደላዊት ማርያም
ታየ ። ፲እርስዋ ሄዳ ከእርሱ ጋር ሆነው ለነበሩት ሲያዝኑና
ሲያለቅሱ ሳሉ አወራችላቸው ፤ ፲፩እነርሱም ሕያው እንደ ሆነ
ለእርስዋም እንደ ታየች ሲሰሙ አላመኑም ።

**ኢየሱስ ለሁለቱ ደቀ መዛሙርት ተገለጠ**

፲፪ከዚህም በኋላ ከእነርሱ ለሁለቱ ወደ ባላገር ሲሄዱ
በመንገድ በሌላ መልክ ተገለጠ ፤ ፲፫እነርሱም ሄደው ለሌሎቹ
አወሩ ፤ እነዚያንም ደግሞ አላመኑአቸውም ።

**ኢየሱስ ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት የሰጠው ትእዛዝ**

፲፬ኋላም በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ ለአሥራ አንዱ ተገ
ለጠ ፣ ተነሥቶም ያዩትን ስላላመኑአቸው አለማመናቸውንና
የልባቸውን ጥንካሬ ነቀፈ ። ፲፭እንዲህም አላቸው ፦ ወደ ዓለም
ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ። ፲፮ያመነ የተ
ጠመቀም ይድናል ፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል ። ፲፯ያመኑት
ንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል ፤ በስሜ አጋንንትን
ያወጣሉ ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ ፤ ፲፰እባቦችን ይይዛሉ ፣ የሚ
ገድልም ነገር ቢጠጡ አይጐዳቸውም ፤ እጃቸውን በድውዮች
ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ ።

**የኢየሱስ እርገት**

፲፱ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማ
ይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ ። ፳እነርሱም ወጥ
ተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ ፣ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ
ነበር ፣ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር ።



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ደ

### ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org